## የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከወጣ ፡ ከአሥር ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ስለሚፈጸም ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ሁኔታ ።

ከጆን ፡ ኤች ፡ ቤክስትሮም ፤

የኢትዮጵያን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ያዘጋጁት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሬኔ ፡ ዴቪድ ፡ ያረቀቁት ፡ ሕግ ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚነሱትን ፡ የጋብቻ ፡ ክርክሮች ፡ ለመወሰን ፡ ላላ ፡ ያለ ፡ ዘዴ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ያሰቡትን ፡ ነው ።[1] እሳቸውም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚነሱትን ፡ የጋብቻ ፡ ክርክሮች ፡ ለመወሰን ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ልማድ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ በቂና ፡ ትክክለኛ ፡ እውቀት ፡ የሌላቸው ፡ መሆኑን ፡ አልካዱም። ኢትዮጵያውያን ፡ ምሁራን ፡ እንኳ ፡ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፤ በዘር ፡ በሃይማኖትና ፡ በጂኦግራፊ ፡ ልዩነት ፡ ላይ ፡ በተመሠረተው ፡ የልማድ ፡ ልዩነት ፡ ምክንያት ፤ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ እንዳለባቸው ፡ ይናገራሉ ።[2] ምንም ፡ እንኳ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዴቪድ ፡ ጕልቶ ፡ የሚታየውን ፡ ያም ፡ ቢቀር ፡ በብዙ ፡ ቦታ ፡ የሚሠራበትን ፡ ክርክር ፡ መወሰኛ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ለይተው ፡ በሕግ ፡ መልክ ፡ ያስቀመጡት ፡ ቢመስላቸውም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ዘዴን ፡ ብቻ ፡ በጠቅላላው ፡ በሀገሪቱ ፡ ላይ ፡ እንዲሠራበት ፡ ለማድረግ ፡ አልሞከሩም ። በዚህም ፡ ምክንያት ፤ ሕጉ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሀሳብ ፡ በማቅረብ ፡ ብቻ ፡ የተወሰነ ፡ ሲሆን ፤ የግድ ፡ መፈጸም ፡ አለባቸው ፡ የሚሏቸው ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ከነዚሁም ፡ ውስጥ ፡ ሊጠቀስ ፡ የሚገባው ፡ የጋብቻ ፡ ክርክሮች ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመቅረባቸው ፡ በፊት ፤ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ ለመረጧቸው ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ መቅረብ ፡ እንዳለባቸው ፡ የሚያዝዘው ፡ ነው ።[3] በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ዘዴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ በሕጉ ፡ በሚገባ ፡ እመጠቀም ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ እንደሚችል ፡ የሕጉ ፡ አዘጋጅ ፡ ተስፋ ፡ አድርገዋል። ይህ ፡ ለውጥ ፡ መቼ ፡ እንደሚሆን ፡ ለመናገር ፡ አስቸጋሪ ፡ እንደሆነና ፤ ምናልባት ፡ በሀገሪቱ ፡ ባለው ፡ የልማድ ፡ ልዩነት ፡ ምክንያት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥፍራዎች ፡ በተለያዩ ፡ ጊዜያት ፡ ሊፈጸም ፡ እንደሚችል ፡ ፕሮፌሰር ፡ ዴቪድ ፡ ተገንዝበውት ፡ ነበር ።[4] ምናልባትም ፡ በተለያዩ ፡ ሥፍራዎች ፡ በተለያየ ፡ አኳኋን ፡ ሊፈጸም ፡ እንደሚችል ፡ ሊናገሩ ፡ ይችሉ ፡ ነበር ።

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ በታላላቅ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፤ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ በሚነሱ ፡ ክርክሮች ፡ ረገድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በዋለበት ፡ የአሥር ፡ ዓመታት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ስላደረገው ፡ ለውጥ ፡ መግለጫ ፡ ለማቅረብ ፡ ነው። በተጨማሪም ፡ በከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ የሚነሱትን ፡ የጋብቻ ፡ ክርክሮች ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከሚታየው ፡ የማሕበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ በኩል ፡ ለመመልከት ፡ እንሞክራለን።

---

1. አር ፡ ዳቪድ ፤ ለ ፡ ድሯ ፡ ደ ፡ ላ ፡ ፋሚይ ፡ ዳን ፡ ለ ፡ ኮድ ፡ ሲቪል ፡ ኢትዮፒየን ፤ ፲፱፻፷ ፤ ገጽ ፡ ፯ ።
2. ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፫ ።
3. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፲፻፸፭ ፤ ፲፻፴፯ ፤
4. አር ፡ ዳቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጽ ፡ ፯ ፡ ይመለከቷል ፤

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፤ ሦስት ፡ ከፍተኛ ፡ ከተሞች ፡- አዲስ ፡ አበባ ፤ አሥመራና፡ ሐረር ፡- እና ፡ አካባቢያቸው ፡ በሰፊው ፡ ተጠንተዋል ። ለዚሁም ፡ ጥናት ፤ ያለልዩ ፡ ዘዴ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ አሥር ፡ የጋብቻ ፡ ክርክሮች ፡ የተመረጡ ፡ ሲሆን ፤ የያንዳንዳቸ ውም ፡ ጥናት ፡ የተከናወነው ፡ የጋብቻውን ፡ ክርክር ፡ በመወሰን ፡ ረገድ ፡ ተካፋይ ፡ ከሆኑት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ለአንዱ ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ በማቅረብ ፡ ነበር ። በተጨማሪም ፤ በጋብቻ ፡ ክርክሮች ፡ በቂ ፡ ልምድ ፡ ያላቸው ፡ ፴ ፡ ጠበቆች ፡ የቃል ፡ ጥያቄ ፡ ተደርጐላቸዋል ። እንዲሁም ፤ በጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የተነሱ ፡ ስልሳ ፡ አምስት ፡ የክር ክር ፡ ፋይሎች ፡ ተጠንተዋል ። በመጨረሻም ፤ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ያለውን ፡ አስተያየታ ቸውን ፡ በዚሁ ፡ ጥናት ፡ ማጠናቀር ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፡ ከብዙ ፡ ዳኞችና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሠራተኞች ፡ ጋር ፡ ውይይት ፡ ተደርጓል ።

ጽሑፉ ፡ ለሁለት ፡ የተከፈለ ፡ ነው ። የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፤ ቤተሰብን ፡ ስለ ሚመለከቱ ፡ ክርክሮች ፡ መፍትሔና ፡ ሕጋዊና ፡ ማኅበራዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ ለሚገልጸው፡ ለሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ መሠረት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሠፋ ፡ ያሉ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ነክ ፡ አስተያየቶችን ፡ የያዘ ፡ ነው ።

## ክፍል ፡ አንድ ፤

## በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚፈጠሩ ፡ የጋብቻ ፡ ክርክሮች ፡ ከአገር ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መምጣት ፤ ጋብቻና ፡ ችግር ፤

ስለኢትዮጵያ ፡ የተደረሱ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ጥናት ፡ ጽሑፎች ፤ በጉዞ ፡ ላይ ፡ የተደረጉ ፡ ወይይቶችና ፡ የመሳሰሉት ፡ ሁሉ ፡ በአለፉት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ አስተያየት ፡ ሰጥተዋል ። ይኸውም ፤ በሀገሪቱ ፡ ውስጥ ፡ በጋብቻ ፡ የሚደረገው ፡ መተሳሰር ፡ እንደቀላል ፡ ነገር ፡ የሚቆጠርና ፡ የፍቺውም ፡ መጠን ፡ ከፍተኛ ፡ መሆኑን ፡ ነው ።[5] ይሁን ፡ እንጂ ፤ እነዚህ ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጽሑፎች ፡ አስ ተያየት ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ያዘለ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፤ የኢትዮጵያን ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ከሌሎች ፡ ጋር ፡ ለማወዳደር ፡ የሚያስችል ፡ የሳይንስ ፡ መረጃ ፡ የላቸውም ።

የቤተሰብ ፡ መተሳሰር ፡ በጣም ፡ የጠነከረ ፡ ነው ፡ በሚባልበት ፡ በገጠሩ ፡ ክፍል፡ እንኳን ፤ በሰውየው ፡ ወይም ፡ በሴቲቱ ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ የሚፈርሱት ፡ ጋብቻዎች፡ ቁጥር ፡ አነስተኛ ፡ መሆኑ ፡ አያጠራጥርም ። "ጋብቻ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በተለየ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚፈጠርን ፡ መተሳሰር ፡ የሚያመለክት ፡ ስለሆነና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚፈጠሩትም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የወንድና ፡ ሴት ፡ ግንኙነቶች ፡ በገሀድ ፡ የማይ ፈጸሙ ፡ ስለሆኑ ፤ ይህንኑ ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ አላስገባውም ።[6] የጋብ

5. ለምሳሌም ፤ አንዳርጋቸው ፡ ተስፋዬ ፡ "የሴትኛ ፡ አዳሪነት ፡ ችግር ፤" (በእንግሊዝኛ ፡ የተጻፈ) ፡ ዩኒቨ ርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፤ የቀድሞ ፡ ተማሪዎች ፡ ማኅበር ፡ መጽሔት ፡ (ቡለቲን) ፤ ቮልዩም ፡ ፩ ፤ ፲፱፻፷፰ ፤ ገጽ ፡ ፴ ፡ ደብልዩ ፡ ሻክ ፤ "ዘ ፡ ጉራጌ" ፤ ፲፱፻፷፮ ፤ ከገጽ ፡ ፹፱—፺ ። ኢ ፡ ሉተር ፤ "ኢትዮጵያ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፤ (በእንግሊዝኛ፡ የተጻፈ) ፡ ፲፱፻፶፰ ፤ ገጽ ፡ ፴፯ ፤ ሃርትልማየር ፤ "ጎልደን ፡ ላየን" ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ገጽ ፡ ፴፯። ታልቦት ፡ "ኮንቴምፖራሪ ፡ ኢትዮፒያ" ፡ ፲፱፻፶፪ ፤ ገጽ ፡ ፺፯ ።

6. "በ ፡ ደሞዝ" ፡ በሚል ፡ ስም ፡ የታወቀው ፤ ሴት ፡ በወር ፡ በወር ፡ በሚታሰብ ፡ ክፍያ ፡ እንደ ፡ ቤት ጠባ ቂና ፡ እንደ ፡ ሚስት ፡ የምትቀጠርበት ፡ ሥርዓት ፡ "ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ስለ ፡ መኖር" ፤ በሚለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አርእስት ፡ (ምዕራፍ ፡ ፰) ፡ ስር ፡ መጠነኛ ፡ ሕጋዊ ፡ ተደማጭነትን ፡ አግኝቷል ።

ቻ ፡ መፍረስ ፡ (ፍቺ) ፡ የሚለው ፡ ቃልም ፡ በድርሰቲቱ ፡ ውስጥ ፡ በተጠቀሰ ፡ ጊዜ ፤ ሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ መግለጫ ፡ ካልተሰጠ ፡ በቀር ፤ የሚያሳየው ፡ (የሚገልጸው ፡) በተለየ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጠረ ፡ ግንኙነት ፡ በተመሳሳይ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መፍረሱን ፡ ነው ።

ባለፉት ፡ ጊዜያት ፤ በባላገሩ ፡ ውስጥ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ የተለመደ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፤ የከተማዎች ፡ እድገት ፡ ይህንኑ ፡ ሁኔታ ፡ አባብሶታል ። ወጣት ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፤ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ይገጥመናል ፡ ብለው ፡ ባለሙት ፡ ተስፋ ፡ ተደልለው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ በመምጣት ፡ የቤተሰቦቻቸውን ፡ መኖር ፡ ከንጭራሹ ፡ እስከመርሳት ፡ ደርሰዋል ።[7]

ከተማም ፡ ውስጥ ፡ ወጣቱ ፤ በዘር ፡ በሃይማኖትም ፡ ሆነ ፡ በኤኮኖሚ ፡ ከማይመሳሰለው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ይመሠርታል ። ይህን ፡ የመሰለም ፡ የተለያየ ፡ ግንኙነት ፡ የመመስረት ፡ ዕድልም ፤ በከተማም ፡ ውስጥ ፡ ተወልዶ ፡ ላደገው ፡ ወጣትም ፡ ቢሆን ፡ ክፍት ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ዓይነቱም ፡ ውጥንቅጥ ፡ ግንኙነት ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ተመሳሳይ ፡ ከሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ከሚደረገው ፡ ግንኙነት ፡ ጋር ፡ ሲወዳደር ፡ የዘላቂነት ፡ ዕድሉ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቻላል ።

የከተማው ፡ ባላገር ፡ ከጓደኛው ፡ ጋር ፡ የከተማ ፡ ኑሮውን ፡ እንደመሠረተ ፤ ገጠር ፡ ከቀረው ፡ ጓደኛው ፡ የበለጠ ፡ ብቸኝነትና ፡ ነፃነት ፡ ይሰማዋል ። በአንድ ፡ በኩል ፤ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ጓደኛው ፡ ጋር ፡ ስላለው ፡ ግንኙነት ፡ ከቤተሰብ ፡ ቁጥጥርና ፡ ትዝብት ፡ ነፃ ፡ መሆኑ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሲሰጠው ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ፤ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ጭቅጭቅ ፡ በተነሳ ፡ ጊዜ ፡ ሊረዱት ፡ የሚችሉት ፡ የቅርብ ፡ ጓደኞቹን ፡ በቀላሉ ፡ ሊያገኛቸው ፡ ባለመቻሉ ፡ ብስጭት ፡ ሊያድርበት ፡ ይችላል ።

በቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚነሱ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ከፍተኛ ፡ ችግሮችንም ፡ ያለእርዳታ፡ ለማለፍ ፡ የሚችሉ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።[8] ከጓደኛው ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፤ ወረቱ፡ እንዳለቀለትም ፡ ወጣቱ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ በብዛት ፡ በሚገኙት ፡ በጠጅና ፡ ጠላ ፡

---

7. ኤች ፡ ካስል ፤ "በኢትዮጵያ ፡ ስለሕፃናት ፡ ፍላጐት ፡ የተደረገ ፡ ጥናት ፤" ፲፱፻፶፰ ፤ ያልታተመ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ጥናትና ፡ ምርመራ ፡ ኢንስቲትዩት ፤ ቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ ገጽ ፡ ፴፩ና ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ኮሌጅ ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤትና ፡ የአፍሪካ ፡ ኤኮኖሚክ ፡ ኮሚሽን ፤ "የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ጥናት ፤" ፲፱፻፶፱ ፤ ገጽ ፡ ፳፯ ፡ ይመለከቷል ።
ስለ ፡ ከተማዎች ፡ የመማረክ ፡ ኃይል ፡ በአንዲት ፡ ሴት ፡ የተሰጠውን ፡ አስተያየት ፤ "ዘ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሄራልድ ፤" ሰኔ ፡ ፳፰/፲፱፻፷፩ ፤ ገጽ ፡ ፫ ፤ ፩ኛ ፡ ዓምድ ፡ ላይ ፡ ተጠቃሎ ፡ ይገኛል ፤ "በአንድ ፡ ገጠሬ ፡ ሕብረ ፡ ሰብ ፡ ውስጥ ፡ ተወለድሁ ፤ በዘጠኝ ፡ ዓመቴ ፡ አገባሁ ፤ በአስረኛው ፡ ላይ ፡ የመጀመሪያ ፡ ልጄን ፡ ወለድሁ ፤ በትዳሬ ፡ ተመረርሁ ፡ ----" በከተማ ፡ ሕይወት ፡ ብልጭልጭ ፡ ነገሮች ፡ ተደልላ ፡ ደስታንና ፡ "ጥሩ ፡ ኑሮን ፡" ለመፈለግ ፡ ቤቷን ፡ ዘግታ ፤ ከዘመዶችዋ ፡ ተነጥላ ፡ መንከራተት ፡ የጀመረችው ፡ ኮረዳ ፡ አሳዛኝ ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ይጀምራል ። በዚህም ፡ ፋንታ ፡ የሚገጥማት ፤ በዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ የማስታወቂያ ፡ ክፍል ፡ እየተዘጋጀ ፡ በሚቀርበው ፡ የአማርኛው ፡ እድገት ፡ መጽሔት ፡ እንደተገለጸው ፤ አስቃቂ ፡ አሳዛኝና ፡ አወላዋይ ፡ በእድል ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ዓለም ፡ ይሆንና ፡ ከተወናበደችበት ፡ መንፈስዋ ፡ ያነቃታል ፤ ---ጽሑፉ ፤ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ በቀላሉ ፡ ተጀምሮ ፡ በፍጥነት ፡ ወደሚያድግ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ችግር ፡ ለሚለወጠው ፡ የተለመደ ፡ የሕይወት ፡ ዘዬ ፡ መጠነኛ ፡ መግቢያ ፡ ይሰጣል ።"

8. በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በዛምቢያ ፡ (ያኔ ፡ ሰሜን ፡ ሮዴሺያ) ፤ ውስጥ ፡ ስለነበረው ፡ ሁኔታ ፡ የተሰጠውን ፤ "የጋብቻ ፡ አለመጽናት ፡ ከገጠር ፡ ይልቅ ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ በርክቶ ፡ ይገኛል ፤" የሚለውን ፡ አስተያየት ፡ ያወዳድሯል ። ይህንም ፡ ሁኔታ ፡ "በከተማ ፡ ውስጥ ፡ የባህል ፡ ቁጥጥር ፡ አለመኖር ፤ የሴቶች፡ ሥራ ፡ ፈትነት ፡ (ስንፍና) ፡ ለፍትወተ ፡ ሥጋ ፡ ያላቸውን ፡ ፍላጐት ፡ ስለሚያነሳሳው ፤ የሴቶቹና ፡ የወንዶቹ ፡ ቁጥር ፡ አለመመጣጠን ፤ እና ፡ በነገዶች ፡ መካከል ፡ ከሚደረጉት ፡ ጋብቻዎች ፡ ጋር ፡ "አዛምዶውታል ። ሳውዘል ፤ (አዘጋጅ) ፡ "በዘመናዊ ፡ አፍሪካ ፡ ውስጥ ፡ ስላለው ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ለውጥ፤" (በእንግሊዝኛ ፡ የተጻፈ) ፡ ፲፱፻፶፫ ፤ ገጽ ፡ ፫፻፳፯ ።

ቤቶች ፡ መጠጥ ፡ በመውሰድና ፡ ሌሎች ፡ ነገሮችንም ፡ በመሻት ፡ ጊዜውን ፡ ያሳልፋል ። ለጥናታችን ፡ ከቀረቡትና ፡ የባልየው ፡ ጥፋት ፡ ጕልቶ ፡ በታየባቸው ፡ የጋብቻ፡ ጉዳይ ፡ ችግሮች ፡ ውስጥ ፡ ለብዙዎቹ ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ የተገኘው ፡ የነዚህ ፡ መጠጥ ቤቶች ፡ መኖር ፡ ወይም ፡ የባልየው ፡ ከሌላ ፡ ሴት ፡ (ከቅምጡ) ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ዘላቂ፡ ወዳጅነት ፡ መሆኑ ፡ ተደርሶበታል ።[9]

በትዳር ፡ ሴቶችም ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፤ እነዚህ ፡ ቤቶች ፡ ትልቅ ፡ የመደለል ፡ ኃይል ፡ እንዳላቸው ፡ ታውቆአል ። ወጣት ፡ ሴቶች ፤ በነዚህ ፡ ንግድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሴቶች ፡ ከነርሱ ፡ ይበልጥ ፡ ሲለብሱና ፡ ሲብለጨለጩ ፤ በተመለከቱ ፡ ጊዜ ፡ እኒህን ፡ መሰል ፡ ሱቆችን ፡ ለማቋቋምና ፡ እራሳቸውን ፡ ከእህቶቻቸው ፡ እኩል ፡ ለማድረግ ፡ ሲሉ ፡ ከባሎቻቸው ፡ ይነጠላሉ ።[10]

በታላላቅ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ በሚፈጠሩ ፡ በእንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ችግሮችና ፤ በየትኛውም ፡ አገር ፡ በከተማም ፡ ሆነ ፡ በገጠር ፡ በሚገኙ ፡ ባለትዳሮች ፡ ላይ ፡ በሚደርሱ ፡ ተመሳሳይ ፡ ችግሮች ፡ ምክንያት ፡ ማንኛውም ፡ ትዳር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ መናጋቱ፡ አይቀርም ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ይፈጠራል ። ጥፋተኛው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ተጣራም ፡ አልተጣራም ፤ ወይም ፡ የመለያየት ፡ ፍላጎት ፡ ያለው፡ ማንኛው ፡ ወገን ፡ እንደሆነ ፡ ተለየም ፡ አልተለየም ፤ ሴቲቱ ፡ ቤቷን ፡ ትታ ፡ ከዘመዶችዋ ፡ ወይም ፡ ከጓደኞችዋ ፡ ጋር ፡ ለመቀመጥ ፡ መሄድዋ ፡ የተለመደ ፡ ነው ።[11] ወንድየውም ፡ እቤቱ ፡ ተቀምጠ ፡ ሚስቱን ፡ ማባረር ፡ እንደልዩ ፡ መብቱ ፡ የሚመለከተውና ፡ የሚኮራበትም ፡ ነገር ፡ ነው ።[12] ይህም ፡ ሥልጣን ፡ ለወንድየው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅምን ፡ ይሰጠዋል ። ምክንያቱም ፡ ሴቲቱ ፡ በምትሄድበት ፡ ጊዜ ፡ ተሸክማው ፡ ልትሄድ ፡ ከምትችለው ፡ ጥቂት ፡ ዕቃ ፡ በስተቀር ፡ መላው ፡ የቤት ፡ ንብረት ፡ በባልየው ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ስለሚውልና ፡ በዚህም ፡ የተነሳ ፡ ምናልባት ፡ ባልየው ፡ ለመፍታትም ፡ ሆነ ፡ በትዳሩ ፡ ለመጽናት ፡ ያለው ፡ ፍላጐት ፡ ግልጽ ካልሆነ ፤ የሚቀጥለው ፡ ማናቸውም ፡ እርምጃ ፡ ከሴቲቱ ፡ የሚጠበቅ ፡ ይሆናል ።

---

9. "ዘ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሄራልድ ፡" ግንቦት ፡ ፳፮ ፤ ፲፱፻፷፩ ፤ በገጽ ፡ ፯ ፤ ፫ኛ ፡ ዓምድ ፡ ላይ ፡ አቶ ፡ በላይ ፡ ጥላሁን ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሬጅስትራር ፡ የሰጡትን ፡ ኢንተርቪው ፡ (የቃል ፡ ጥያቄ) በተጨማሪ ፡ ይመለከቷል ፤ "ጋብቻዎች ፡ የፈረሱባቸውን ፡ ነገሮች ፡ መዝገብ ፡ በየቀበሌዎቹ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከተመለከቱ ፡ በኋላ ፤ በሞራል ፡ ውድቀት ፡ ሴቶችም ፡ ወንዶችም ፡ የሚወቀሱ ፡ መሆናቸው ፡ ያሳዝናል ።----ላቅ ፡ ባለ ፡ መጠን ፡ የተለመደው ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ ግዴለሽነት ፡ ነው ። ብዙዎቹ ፡ ወንዶች ፡ ለቤተሰባቸው ፡ ፍጹም ፡ ግዴለሽ ፡ ከመሆናቸው ፡ በላይ ፤ ወደቤታቸው ፡ በመሄድ፡ ፋንታ ፡ ወደየመጠጥ ፡ ቤቱ ፡ እዘውትረው ፡ የሚሄዱ ፡ ናቸው ።----እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ደሞዛቸውን ፡ ካልተጋቡ ፡ ሴቶች ፡ ጋር ፡ ሆነው ፡ ማባከናቸው ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ——ትዳራቸውን ፡ በማፍረስ ፡ ረገድ ፡ ሴቶችም ፡ ቢሆኑ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ሊወቀሱ ፡ ይገባል ።---- ሴቶቹ ፡ የከንፈር ፡ ወዳጅ ፡ በያዙ ፡ ጊዜ ፡ ባሎቻቸውን ፡ በጣም ፡ ያሰቃይዋቸዋል ።"

10. አንዳርጋቸው ፡ ተስፋዬ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጽ ፡ ፴፬ ፡ ይመለከቷል ። ደራሲው ፤ ካጠኗቸው ፡ ፫፻ ፡ የቡና ፡ ቤት ፡ ሴቶች ፡ ዘጠና ፡ አምስት ፡ በመቶ ፡ የሚሆኑት ፡ ፈቶች ፡ መሆናቸውንና ፤ ብዙዎቹም ፡ ከአንድ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ አግብተው ፡ የፈቱ ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጸዋል ። ከዚያው ፡ ገጽ ፡ ፴ ። በተጨማሪም ፤ ቢ ፡ ሻተርጂ ፤ "የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ደኅንነትና ፡ የኅብረ ፡ ሰብ ፡ እድገት ፡ በኢትዮጵያ ፤" (በእንግሊዝኛ ፡ የተጻፈ) (፲፱፻፶፱) ገጽ ፡ ፳፪ ፤ ይመለከቷል ፤ "ቁጥራቸው ፡ እጅግ፡ እየበረከተ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ የቡና ፡ ቤቶችና ፡ የመጠጥ ፡ ቤቶች ፡ የመሳብ ፡ ኃይል ፡ መቀነስ ፡ ስንችል ፤ በፍቅርና ፡ በደስታ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ጽኑ ፡ የቤተሰብ ፡ ሕይወት ፡ ለመፍጠር ፡ የበለጠ ፡ እድል ፡ ይኖራል ።"

11. ለዓይነት ፡ ያጠናነው ፡ ይህንኑ ፡ ገልጿል ። የተከበሩ ፡ ሻለቃ ፡ በቀለ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤልና ፡ የተከበሩ ፡ አቶ ፡ ታደሰ ፡ ጉርሙ ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዳኞች ፤ ግንቦት ፡ ፯/፲፱፻፷፩ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ፡ በሰጡት ፡ ኢንተርቪው ፡ ይህንኑ ፡ ገልፀዋል ።

12. ሁለት ፡ በመቶ ፡ የሚሆኑት ፡ በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የተጀመሩ ፡ ናቸው ።

በጥናታችን ፡ እንደተገለጸው ፤ በኢትዮጵያ ፡ ከተማዎች ፡ የጋብቻን ፡ ጉዳይ ፡ ችግሮች ፡ ከሚመለከቱት ፡ ክሶች ፡ ዘጠና ፡ በመቶው ፡ በሴቲቱ ፡ የሚጀመሩ ፡ ናቸው ።[13]

## <u>እርቅ ፡ ፍቺና ፡ ያለ ፡ ልዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መለያየት ፤</u>

ምንም ፡ እንኳ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ባይኖርም ፤ ይህን ፡ የመሰሉት ፡ ክሶች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ እርቅ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ናቸው ።[14] ካጠናናቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ሰውየው ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ በተገኘባቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ለሴቲቱ ፡ የልብስ ፡ ወይም ፡ የጌጣጌጥ ፡ ካሣን ፡ እንዲሰጥ ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ ይጠየቃል ።

የጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ ችግር ፡ ተፈጥሮ ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ አማካይነት ፡ በእርቅ ፡ የተፈጸሙት ፡ ጋብቻዎች ፡ በሞላ ፡ ጐደል ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ተኩል ፡ ያህል ፡ የቆዩ ፡ ጋብቻዎች ፡ ሲሆኑ ፤ በፍቺ ፡ ውሳኔ ፡ የተፈጸሙት ፡ ጋብቻዎች ፡ ደግሞ ፡ የዘጠኝ ፡ ከ፩/፫ኛ ዓመታት ፡ ዕድሜ ፡ እንዳላቸው ፡ ተደርሶበታል ። ይህም ፡ የሚያስረዳው ፤ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ ለመቆየት ፡ የቻሉ ፡ ባለትዳሮች ፡ እያለፈ ፡ ሊገጥማቸው ፡ የሚችለውን ፡ ያለመስማማት ፡ የማሸነፍ ፡ ዕድላቸው ፡ ከሌሎች ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ ነው ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስላለው ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ሁኔታዎች ፡ ጥናት ፡ አስፈላጊ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ይኸን ፡ መሰሉ ፡ ጥናት ፡ በቅርቡ ፡ እንደሚደረግ ፡ ተስፋ፡ አለን ።[15] የተጠቃለለ ፡ ዝርዝር ፡ ጥናት ፡ (ስታቲስቲክስ) ፡ ሳይኖረን ፤ የጋብቻ ፡ መፍረስን ፡ የተመለከቱ ፡ ሠላሳ ፡ ጠበቆች ፡ በገለጹልን ፡ ሀሳብ ፡ (በተለይም ፤ እንደማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ግላዊ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ከመስንዘር ፡ ስለማይቆጠቡ) ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አጠቃላይ ፡ መግለጫ ፡ መስጠት ፡ አስቸጋሪ ፡ ይሆናል ። ጠበቆቹ ፤ በከተማው ውስጥ ፡ ከተፈጸሙት ፤ እነሱ ፡ ከሚያውቋቸው ፡ ሕጋዊ ፡ ጋብቻዎች ፡ ውስጥ ፤ ሕጋዊ ፡

---

13. ለዓይነት ፡ ያደረግነው ፡ ምርጫ ፡ በዘፈቀደ ፡ የተደረገ ፡ በመሆኑና ፤ ጥናቱም ፡ በብዛት ፡ የተከናወነው ፡ ከረር ፡ ያሉት ፡ ችግሮች ፡ በሚገኙበት ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ቅጽር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ስለሆነ ፤ ካጠናናቸው፡ ከ፳፩ቱ ፡ የፍቺና ፡ ከ፴፰ቱ ፡ የእርቅ ፡ ሁናቴዎች ፡ ሊወጣጣ ፡ የሚችል ፡ መደምደሚያ ፡ አይኖርም ።

14.] ይኸም ፡ ሰባ ፡ አራት ፡ በመቶ ፡ የሚሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

15. በቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ በሕክምና ፡ ፋክልቲ ፡ ውስጥ ፡ የሳይካትሪ ፡ ሜዲሲን ፡ ተባባሪ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ከሆኑት ፤ ከዶክተር ፡ አር ፡ ጓየል ፡ ጋር ፡ የተደረገ ፡ አንድ ፡ ውይይት ፤ <u>በአዲስ ፡ ሪፖርተር</u> ፤ ሰኔ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱፻፷፩ ፤ በገጽ ፡ ፲፬ ፡ ላይ ፤ በአዋቂዎች ፡ መካከል፡ የተከናወነ ፡ (አንድ ፡ ጥናት ፡ ገልጿል) ። ከዚህ፡ ቀደም ፡ ያገቡ ፤ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ሁኔታ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ውስጥ ፡ ሃምሳ ፡ በመቶው ፤ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ የአንድ ፡ ጊዜ ፡ የፍቺ ፡ ታሪክ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ። አሥራ ፡ ሁለት ፡ በመቶው ፡ ደግሞ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ የተፋቱ ፡ ናቸው ።" ይህ ፡ ጥናት ፡ የት ፡ እንደተከናወነ ፤ ወይም ፡ ለዓይነት ፡ የተጠኑት ፡ ሁኔታዎች ፡ እንዴት ፡ እንደተመረጡ ፡ የሚገልጽ ፡ መረጃ ፡ ለማግኘት ፡ አልተቻለም ። በተጨማሪም ፤ "ዘ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሄራልድ ፤" የካቲት ፡ ፳፬/፲፱፻፷፩ ፤ ገጽ ፡ ፪ ፤ በ፬ኛው ፡ ዓምድ ፡ ላይ ፤ የሠፈረውን ፤ "ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ በስምምነት ፡ የሚደረጉም ፡ መለያየቶች ፡ መጠናቸው ፡ ከሚያስደነግጥ ፡ ደረጃ ፡ ደርሷል ። ከእያንዳንዱ ፡ አስር ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ ብቻ፡ እውነተኛ ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል ፤" ጽሑፍ ፡ ይመለከቷል ። ይህ ፡ ግምት ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ እንደተገኘ ፡ አልተገለጸም ።

ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ የተጠቀሰውን ፤ "<u>የአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አቋም ፡ ጥናት ፤</u>" በገጽ ፡ ፳፪ ፡ ላይ ፡ የሠፈረውን ፤ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ውስጥ ፡ "የተለያዩና ፡ የተፋቱ ፡ ሴቶች ፡ ቁጥር ፡ የበዛው ፡ በቀጨኔና ፡ በሾላ ፡ (ቀበሌ) ፡ ሲሆን ፤ የሁኔታውም ፡ መደጋገም ፡ ልክ ፡ በእያንዳንድዋ፡ ያገባች ፡ ሴት፡ መጠን ፡ 0.86 ፡ ደርሷል ፤ እንዲሁም ፡ በልደታ ፡ (ቀበሌ) ፡ የልኩ ፡ መጠን ፡ —0.8 ፡ ሆንዋል። በዚህ ፡ ይዞታ ፡ በጣም ፡ ሀብታም ፡ የሆኑት ፡ ቀበሌዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው" ። በተጨማሪም ፤ ቢ ፡ ሻተርጂ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፭ ፡ የተጠቀሰውን ፤ በገጽ ፡ ፳ ፡ የተገለጸውን ፤ አዲስ ፡ አበባንና ፡ አሥመራን ፡ ሳይጨምር፡ በ፲፱ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፤ የተፋቱ ፡ ማዕከላዊ ፡ ቁጥር ፡ በመቶ ፡ 16.3 ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ይመለከቷል ። ለሐረር ፡ የተሰጠው ፡ ቁጥር ፡ በመቶ ፡ 8.6 ፡ ነው ።

በሆነ ፡ መንገድ ፡ የፈረሱት ፡ ጋብቻዎች ፡ ፳፰ ፡ በመቶ ፡ እንደሚደርሱ ፡ ገምተዋል ። በጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ላይ ፡ ከሃይማኖት ፡ በኩል ፡ በሚሰነዘረው ፡ ትችት ፡ ምክንያት ፣ ከእነዚህ ፡ ተመልካቾች ፡ የተሰጡን ፡ ግምቶች ፡ እምነት ፡ የሚጣልባቸው ፡ ሆነው ፡ አላገኘናቸውም ።[16] በተጨማሪም ፡ እነዚህ ፡ ግምቶች ፡ ከሁለት ፡ ከሶስት ፡ ወይም ፡ ከአራት ፡ ጋብቻ ፡ በኋላ ፣ ትዳራቸው ፡ ባለመሳካቱ ፡ የእርጅና ፡ ጊዜያቸውን ፡ በሰላም፡ ለማሳለፍ ፡ የሚፈልጉትን ፡ ይጨምራሉ ።

ዳግም ፣ ከላይ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ አስተያየቶች ፡ ጋር ፡ ሊደመር ፡ የሚገባው ፣ ለቃል፡ ጥያቄዎቹ ፡ የተሰጡት ፡ መልሶች ፡ አጠቃላይ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ የገለጹት ፣ "ብዙ ዎች ፡" በሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ የተቆራኙ ፡ ባለትዳሮች ፣ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በጐደለው ፡ መንገድ ፡ እንደሚለያዩና ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜም ፡ ሌላ ፡ ግንኙነት ፡ እንደሚመሠርቱ ፡ ነው ። ሦስት ፡ ጠበቆችም ፣ በዚሁ ፡ ዘዴ ፡ የሚፈጸመው ፡ "መለያየት" ፡ በቤት ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ከሚፈጸመው ፡ ሕጋዊ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ይበልጥ ፡ የሚዘወተር ፡ ነው ፡ እስከማለት ፡ ደርሰዋል ። ይኸ ፡ ዓይነቱ ፡ ያለ ፡ ልዩ ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ የሚደረገው ፡ መለያየት ፡ ባለትዳሮቹ ፡ የንብረታቸውን ፡ ክፍያና ፡ የልጆቻቸው፡ ጥበቃ ፡ የሚመለከተውን ፡ ጉዳይ ፡ በስምምነት ፡ ራሳቸው ፡ ለማስወገድ ፡ ሲችሉ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ለእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ቀላል ፡ ጉዳዮችም ፡ የሌሎችን ፡ እርዳታ ፡ አይፈልጉም ። የፍቺው ፡ ሕጋዊ ፡ መሆን ፡ አለመሆን ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ እንደቀ ላል ፡ ነገር ፡ የሚቆጥሩት ፡ ነው ።

አንድ ፡ ጠበቃ ፡ እንዳሳሰበው ፡ ይህ ፡ ያለ ፡ ደንበኛ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚደረ ገው ፡ መለያየት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሀብታቸው ፡ መጠን ፡ ዝቅተኛ ፡ በሆነ ፡ ባለትዳ ሮች ፡ መሀል ፡ ነው ፣ ምክንያቱም ፡ በእነዚህ ፡ ባለትዳሮች ፡ ዘንድ ፡ የሚፈጠረው ፡ የንብረት ፡ መከፋፈል ፡ ችግር ፡ ብዙ ፡ የማያከራክር ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ባለትዳሮቹ ፡ ተለያይተው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ በአብዛኛው ፡ ንብረታ ቸው ፡ ላይ ፡ እንደገና ፡ ክርክር ፡ ይጀምራሉ ።[17] ይህ ፡ በሚሆንበትም ፡ ጊዜ ፣ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ንብረታቸውን ፡ ከመካፈላቸው ፡ በፊት ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ የፍቺ ፡ ውሳኔ ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ ካለው፡ ክፍል ፡ ይህንኑ ፡ ውሳኔ ፡ ማግኘት ፡ እንዳለባቸው ፡ ለሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ይነግራቸ ዋል ።[18]

ያለ ፡ ደንበኛ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መለያየት ፡ ለጊዜው ፡ አብረው ፡ ለመኖር ፡ ለማ ይሹ ፣ በኋላ ፡ ግን ፡ ብቻቸውንም ፡ ሆነ ፡ ከአዲስ ፡ የትዳር ፡ ጓደኛ ፡ ጋር ፡ ቆይተው ፡ ማንኛውንም ፡ ነገር ፡ ካዩ ፡ በኋላ ፡ የቀድሞው ፡ ጓደኛቸው ፡ እስከዚህም ፡ ድረስ ፡ መጥፎ ፡ አለመሆኑን ፡ ለሚረዱ ፡ ባለትዳሮች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ያስገኛል ። ከጥናታ ችን ፡ እንደተረዳነው ፣ ብዙዎች ፡ ባለትዳሮች ፡ ያለ ፡ ደንበኛ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሲለ

---

16. ታልቦት ፣ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ገጽ ፡ ፶፯ ፡ ይመለከቷል ።

17. ለምሳሌም ፣ የከሳሽ  የምንትዋብ ፡ ተዘራንና ፡ የተከሳሽ ፡ የኋላ ፡ እሸት  ዳምጤን ፡ ነገር ፡ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፣ አዲስ ፡ አበባ ፣ ፲፱፻፶፯ ፣ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፹፩/፺፮ ፡ (ያልታተመ) ይመለከቷል ። (ባለጉዳዮቹ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ተለያይተው፡ ተቀምጠዋል ።) ከሐረር ፡ በተገኘ ፣ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ባጠናነው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፣ ባለጉዳዮቹ ፡ ለ፲፱ ፡ ወር ፡ ተለያይተው ፡ ከመቆየታቸው ፡ በላይ ፣ ባልየው ፡ ሚስቱ ፡ የከስ ፡ ማመልከቻውን ፡ ከማቅረብዋ ፡ በፊት ፡ ሌላ ፡ ሴት ፡ አግብቷል ።

18. ለምሳሌም ፣ የከሳሽ ፡ ጥሩነሽ ፡ ተክለ ፡ ብርሃንና ፡ የተከሳሽ ፡ የገብሬ ፡ ወልደ ፡ መስቀልን ፡ ነገር ፣ (ከፍ ተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፣ አዲስ ፡ አበባ ፣ ፲፱፻፶፯ ፣ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፷፩/፺፯ ፡ (ያልታ ተመ) ፣ ይመለከቷል ።

ያዩ ፤ ከላይ ፡ በተገለጸው ፡ ዓይነት ፡ ትንሽ ፡ ቆይተው ፡ ለመገናኘት ፡ ስለሆነ ፡ እንደ ገና ፡ ተመልሰው ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ለመኖር ፡ በሚፈልጉበት ፡ ጊዜ ፤ ጋብቻው ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ የፈረሰ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እንደገና ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ ለመጋባት ፡ ያለባቸውን ፡ ግዴታ ፡ መፈጸም ፡ አያስፈልጋቸውም ። የአንድ ፡ ሰው ፡ የጋብቻ ፡ ሁኔታ ፡ ሕጋዊነት ፡ በኅብረተሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ስሙን ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ባልሆነበት ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዓይነት ፡ ኅብረተሰብ ፡ ውስጥ ፡ ከሕጋዊው ፡[19] ይልቅ ፡ ያለ ፡ ደንበኛ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መለያየት ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ አለው ። ለዚሁም ፡ ማስረጃው ፡ ያለ ፡ ደንበኛ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መለያየት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ በሰፊው ፡ ሲፈጸም ፡ መታየቱ ፡ ነው ።

## ሃይማኖትና ፡ ሕጉ ፤

በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ የሚፈጸመው ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፤ በአንዳንድ ፡ በተለይ ፡ በተዘረዘሩ ፡ ከባድ ፡ ሁኔታዎች ፡[20] ካልሆነ ፡ በቀር ፤ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ መደበኛ ፡ (ኦፊሲየል) ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሆነችው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ ያላቸው ፡ ተቀባይነት ፡ እጅግም ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ቤተክርስቲያኒቱ ፡ በጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ላይ ፡ ያላት ፡ ተጽዕኖ ፡ ዝቅተኛ ፡ ነው ። ለዚህም ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ቤተክርስቲያኒቱ ፡ የፍቺ ፡ ደንቦችዋን ፡ የምትጠቀምባቸው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በተደረጉ ፡ ጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ እንጅ ፡ በልማድ ፡ ወይም ፡ በሲቪል ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በተደረጉ ፡ ጋብቻዎች ፡ ላይ ፡ ስላልሆነ ፡ ነው ። በከፊልም ፡ ይህንኑ ፡ ምክንያት ፡ በመመርኰዝ ፤ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሆኑ ፡ ተከታዮችዋ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ውስጥ ፡ አይጋቡም ።[21] ይህም ፡ ሁኔታ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኒቱ፡ መወገዝንና ፡ የቅዱስ ፡ ቁርባንን ፡ መከልከል ፡ የሚያስከትል ፡ ቢሆንም ፤[22] በኢትዮጵያውያኑ ፡ ምዕመናን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። የእየሩ ፡ ሁኔታ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ አስደሳች ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፤ ምዕመናኑ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ ግድግዳዎች ፡ አካባቢ ፡ ለመሰብሰብ ፡ ሲችሉ ፤ እያለፈም ፡ የቅዳሴውን ፡ ሥርዓት ፡ በድምጽ ፡ ማጉያ ፡ መሣሪያ ፡ አማካይነት ፡ የመካፈል ፡ ዕድል ፡ አላቸው ።

---

19. አር ፡ ፎርብስ ፤ ከቀይ ፡ ባሕር ፡ እስከ ፡ ጥቁር ፡ አባይ ፤ (በእንግሊዝኛ ፡ የተጻፈ) ፤ (፲፱፻፲፰)፡ ገጽ ፡ ፹፩ ፡ ይመለከቷል ።

20. የሚከተሉት ፤ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የተውጣጡት ፤ በቤተክርስቲያን ፡ ለሚደረገው ፡ የጋብቻ፡ መፍረስ ፡ የተሰጡትን ፡ ምክንያቶች ፤ በ፷ ፡ ማከሪ ፤ "ዘ ፡ ላስት ፡ ኦፍ ፡ ፍሪ ፡ አፍሪካ ፤" (፲፱፻፳) ፤ ገጽ ፡ ፫፻፴፩ና ፤ አር ፡ ፎርበስ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ከገጽ ፡ ፸፰—፹፩ ፡ ይመለከቷል ። ፩ኛ/ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ መነኩሴና ፡ መነኩሲት ፡ ለመሆን ፡ በተስማሙ ፡ ጊዜ ፡ ፪ኛ/ ከሁለት ፡ ያንዳቸው ፡ ልጅ ፡ ለማፍራት ፡ አለመቻል ። ፫ኛ/ታማኝ ፡ አለመሆን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በባልየው ፡ በኩል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ በቂ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ ሕዝብ ፡ ያወቀውና ፡ ወንጀልም ፡ ፈጽመሀል ፡ ለማሰኘት ፡ የሚያስችል ፡ መሆን ፡ አለበት ። ፬ኛ/ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ላይ ፡ የሚያደርገው ፡ የሕይወት ፡ ማጥፋት ፡ ሙከራ ። ፭ኛ/ የሚጥል ፡ ወይም ፡ የባሪያ ፡ በሽታ ፡ (ኤፒለፕሲ) ፡ ከጋብቻ ፡ የተገኘ ፡ ከሆነና ፡ በአንደኛው ፡ ወገን ፡ ችል ፡ የተባለ ፡ ከሆነ ። ፮ኛ/ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በደዌ ፡ ሥጋ ፡ (ቁምጥና) ፡ ወይም ፡ በገጢብ ፡ (የግመል ፡ በሽታ) ፡ የተያዘ ፡ እንደሆነ ፤ ፯ኛ/ አንደኛው ፡ ወገን ፡ የረዥም ፡ ዘመን ፡ እሥራት ፡ የተፈረደበት ፡ እንደሆነ ፤ ፰ኛ/ አንዱ ፡ ወገን ፡ ሌላውን ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ በሐሰት ፡ በዝሙት ፡ ሥራ ፡ የወንጀለው ፡ እንደሆነ ፡ በመጨረሻ ፡ የተጠቀሰው ፡ ምክንያት ፡ በቤተክርስቲያን ፡ ተጋብቶ ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ እንዲታወቅለት ፡ ለሚፈልገው ፡ ወገን ፡ ጥሩ ፡ እድልን ፡ ይከፍቱለታል ።

21. ኤም ፡ ፐርሃም ፤ "የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት" ፤ (በእንግሊዝኛ ፡ የተጻፈ) ፡ (፲፱፻፶) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፲፯ ፡ ይመለከቷል ።

22. ከዚያው ።

በቤተ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ውስጥ ፡ ያልተጋቡ ፡ ባለትዳሮች ፣ አንዳቸው ፡ ወይም ፡ ሁለቱም ፡ የመፍታት ፡ ፍላጐት ፡ ካላቸው ፣ የፍትሐ ፡ ብሔሩን ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓ ታዊ ፡ ግዴታዎች ፡ እስከተከተሉና ፡ ምናልባትም ፡ የንብረት ፡ ማጣትን ፡ ጉዳት ፡ ከቻሉ ፣ ከመፋታት ፡ የሚከለክላቸው ፡ ሕጋዊ ፡ ምክንያት ፡ የለም ።[23] የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ግዴታዎችም ፣ ባለትዳሮቹን ፡ የማስታረቅ ፡ ሙከራ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ጉዳያቸው ፡ እንዲቀርብና ፡ በሽማግሌዎቹም ፡ አማካይነት ፡ ዕርቅ ፡ የማይቻል ፡ ከሆነ ፡ የፍቺ ፡ ብይን ፡ እንዲሰጥ ፡ የሚያዙት ፡ ብቻ፡ ናቸው ።[24] በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ረገድ ፣ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ "በቀላሉ ፡" ጋብቻን ፡ የማፍረስ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደንብ ፡ ለተፈጸሙ ፡ ጋብቻዎችም ፡ የሚያገለግል ፡ ነው ።[25] ለጥናታችን ፡ ከቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ሁለቱ ፡ በአሥ መራ ፡ ከተማ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተደረጉ ፡ ጋብቻዎች ፡ ሲሆኑ ፣ ጋብቻዎቹ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረት ፡ ሲፈርሱ ፡ አንድም ፡ ዓይነት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ተቀብለዋለች ፡ የተባለ ፡ የፍቺ ፡ ምክንያት ፡ አለመጠቀሱ ፡ የሚያ ስገርም ፡ ነው ።[26]

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በተዘጋጀበት ፡ ጊዜ ፣ የእስላም ፡ ሃይማኖት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሕግን ፡ የሚመለከቱ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስንም ፡ የሚጨምሩ ፡ ጥያቄዎች ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የሚመሩ ፡ መሆን ፡ አለመሆናቸው ፣ ወይም ፡ ለዚያው ፡

---

23. የሸዋልዑል ፡ ሃይለማርያምና ፡ የደበበ ፡ ሃይሌን ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከቷል ፣ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፶፱ ፣ የፍትሐብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፳/፶፱) ፡ (በቅርብ ፡ በወጣ ፡ የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ እትም ፡ ውስጥ ፡ የታተመ ።) በተጨማሪም ፣ አር ፡ ዴቪድ ፣ (የኤም ፣ ኪንድረድን ፡ ትርጉም፣) "የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ምንጮች ፣" (በእንግሊዝኛ ፡ የተጻፈ) ፡ የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽ ሔት ፣ ፩ኛው ፡ ቮልዩም ፣ ፲፱፻፶፱ ፣ ገጽ ፡ ፫፻፵፫ ፡ ይመለከቷል ።
24. ከዚያው ፡
25. የዘቢና ፡ የዘቢ ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከቷል ፣ (የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፣ ፲፱፻፶፯ ፣ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ.፩፻፳፱/፶፯) ፡ (ያልታተመ) ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ በማጽናት ፣ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የመፋታት ፡ ጥያቄን ፡ በሚያዩ በት ፡ ጊዜ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ በሃይማኖት ፡ ረገድ ፡ ያላቸውን ፡ አቋም ፣ ወይም ፡ የትውልድ ፡ ሀገራቸውን ፡ መመልከት ፡ አይገባቸውም ፡ ያለ ፡ ይመስላል ። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፣ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግ ልና ፡ ዳኞቹ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለማትፈቅደው ፡ የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ አልፈቀድንም ፡ በማለት ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ የሰጡትን ፡ ውሳኔ ፣ "ከአእምሮ ፡ ሚዛን ፡ ውጭ ፡" ነው ፣ (የፍትሐ ፡ ብሔር ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፴፯) ፡ ብሎ ፡ ሽሮታል ።
26. የትርፌ ፡ መአሾንና ፡ የአብርሽት ፡ ገብረ ፡ መስቀልን ፡ ጉዳይ ፣ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፣ አሥመራ ፣ ፲፱፻፶፱ ፣ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፵፱/፶፱) (በቅርብ ፡ በወጣ ፡ የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ እትም ፡ ውስጥ ፡ የታተመ) ፡ በተጨማሪ ፣ ይመለከቷል ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፣ ፍርድ ፡ ቤቱ ፣ ምንም ፡ እንኳ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ባለሥልጣናት ፡ ደርብ ፡ ለጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ ውሳኔ ፡ ምክንያት ፡ ባያገኙለት ፣ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ የሰጡትን ፡ የመፋታት ፡ ብይን ፡ አጽድ ቆታል ።

በተጨማሪም ፣ ኤም ፡ ማሪየን ፣ "ዘ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ኤምፓየር ፣ ፌዴሬሽን ፡ ኤንድ ፡ ሎውስ ፣" ፲፱፻፵፯ ፣ ገጽ ፡ ፩፻፳፱ ፡ ላይ ፡ ደራሲው ፡ የጠቀሱትን ፣ ከሕጉ ፡ መውጣት ፡ በፊት ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ለተጋቡ ፡ ሰዎች ፡ የሰጠውን ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፣ ይመለ ከቷል ።

ብዙዎች ፡ ወጣቶች ፣ ቁርባንና ፡ እንደ ፡ ሥነ ፡ በዓሉ ፡ ክፍል ፡ ሳያደርጉ ፣ በቤተክርስቲያኒቱ ፡ ውስጥ ፡ መጋባት ፡ መጀመራቸው ፡ ይነገራል ። እነሱም ፣ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ካንዳንድ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የጋብቻ ፡ ጥብቅ ፡ መሠረተ ፡ ሃሳብ ፡- መፋታትን ፡ የሚከለክለውን ፡ ጨምሮ ፡ ነፃ ፡ እንሆናለን ፡ ብለው፡ ይከራከራሉ ። የካቲት ፡ ፪ ፡ ፲፱፻፹፩ ፣ ከልዑል ፡ ሰገድ ፡ በቀለ ፣ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ሕዝብ ፡ ቆጠራና ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ክፍል ፡ ተጠባባቂ ፡ ዲሬክተር ፣ ጋር ፡ የተደረገ ፡ ውይይት ።

ሃይማኖት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ ሕጎች ፡ የተተዉ ፡ መሆናቸው ፡ አልተገለጸም ።[27] በዚህ፡ ጥናት ፡ የእስላም ፡ ሃይማኖትን ፡ የጋብቻ ፡ ቅንጅት ፡ ለማጥናት ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሙከራ ፡ አላደረግንም ። ነገር ፡ ግን ፤ በሐረር ፡ የሚገኝ ፡ አንድ ፡ የእስላም ፡ ሃይማኖት፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ (ናኢባ) ፡ ሁለት ፡ የዚሁ ፡ ሃይማኖት ፡ ባለትዳሮች ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ለጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ የወሰነውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲጠቀሙበት ፡ ሲፈቅድ ፡ ለማየት ፡ ችለናል ።

<u>በቀላሉ ፡ የሚደረግ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡- የሕዝቡ ፡ አስተሳሰብ ፤</u>

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ደራሲ ፡ (አርቃቂ) ፡ ያረቀቁት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተለመደ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሰጡትን ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። መሠረታቸው ፡ የክር ስቲያን ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ ፍልስፍና ፡ በሆኑ ፡ ምክንያቶች ፥[28] "የጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ ሊያስናክሉ ፡ የሚችሉ ፡ ዘዴዎችንም ፡"[29] ጨምረዋል ። እነዚህን ፡ ዘዴዎች ፡ በሚቀ ጥለው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ እንመለከታለን ። ለጊዜው ፡ ዘዴዎቹ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ውሳኔ ፡ በተሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ባልየው ፡ ወይም ፡ ሚስትየዋ ፡ (እንደሁኔታው) ፡ መቀጫ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ለተበዳዩ ፡ ወገን ፡ ከሀብታቸው ፡ እንዲሰጡ ፡ በማድረግ ፡ ባልና ፡ ሚስቱን ፡ እንዳይፋቱ ፡ ለማገድ ፡ የታቀዱ ፡ መሆናቸውን ፡ መግለጽ ፡ ይበቃል። እነዚህ ፡ "የጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ ሊያሰናክሉ ፡ የሚችሉ ፡ ዘዴዎች" ፡ በሃሳብ ፡ (በቲዎሪ)፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፤ ጋብቻን ፡ ማፍረስ ፡ ከሕጉ ፡ በፊት ፡ ከነበረው ፡ ልማዳዊ ፡ ሁኔታ ፡ ይልቅ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ አድርገውታል ።[30]

የቃል ፡ ጥያቄ ፡ ተደርጎላቸው ፡ ከነበሩት፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ በርከት ፡ ያሉትና ፡ ጠበቆቹ ፡ በሙሉ ፡ "በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ጋብቻን ፡ የማፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ ከባድ ፡ ይሁን ፡ አይሁን ፡" ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ አስተያየታቸውን ፡ ለመስጠት፡ ፈቃደኛ ፡ ሆነው ፡ ነበር ። ብዙዎቹም ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ከባድ ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ወደሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ አዘንብለዋል ። ለዚህም ፡ ዝንባሌ ፡ ምክንያት ፡ የአዲሱን ፡ ሕግ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ደጋፊ ፡ መስሎ ፡ ለመታየት ፡ የታቀደ ፡ ምኞት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀ ርም ። በተጨማሪም ፡ ሊጠቀስ ፡ የሚገባው ፤ በአገቡ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ በሃ ሳብ ፡ የመከፋፈል ፡ ዝንባሌ ፤ ማለትም ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ለመፋታት ፡ ባሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ሊከተሉት ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ የሚያምኑበት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፡ እነሱ ፡ እራሳቸው ፡ የጋብቻቸውን ፡ መፍረስ ፡ በሚሹበት ፡ ጊዜ ፡ ልንከተለው ፡ ይገባል ፡ የሚሉት ፡ ሥነ፡ ሥርዓት ፡ የተለያዩ ፡ መሆናቸው ፡ ናቸው ። ካገኘናቸው ፡ መልሶች ፡ በርከት ፡ ያሉት ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓይነት ፡ የአስተሳሰብ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገኙ ፡ አያጠራጥርም።

---

27. አር ፡ ዴቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰውን ፤ ገጽ ፡ ፳፬ ፡ ይመለከቷል ። በዚህም ፡ ደራሲው ፤ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ያልታወጁ ፤ የእስልምና ፡ ሃይማኖት ፡ ተከታዮችን ፡ የሚመለከቱና፡ የፍቺያቸው ፡ ሁኔታ ፡ ጭምር ፡ የሚመራበትን ፡ ረቂቅ ፡ የሕግ ፡ አናቅጽት ፡ ያብራራሉ ።

28. "ይህ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስና ፤ የጋብቻ ፡ አመሠራረት ፡ ሕግ ፤ እኛ ፡ እንደ ፡ ክርስቲያን ፡ ኤውሮፓውያን፡ ሲፈጸም ፡ ልናየው ፡ የምንፈልገው ፡ ዓይነት ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሕጉ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እንጅ ፡ ለቀ ረው ፡ ዓለም ፡ የታሰበ ፡ አይደለም ። "ከዚያው ፤ ከገጽ ፡ ፺፬-፺ ።" የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ በቀላሉ ፡ ለማግ ኘት ፡ እንዳይቻል ፡ ለማድረግ ፡ ያለን ፡ ፍላጎት ፡ በአናቅጽት ፡ ፲፻፺-፲፻፺፭ ውስጥ ፡ ተገልጿል። ከዚያው፡ ገጽ ፡ ፷፩ ።

29. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ" ፤ ቁጥሮች ፡ ፲፻፺—፲፻፺፭ ።

30. ነገር ፡ ግን ፡ ጂ ፡ ማክሪግ ፤ "ዘ ፡ ላስት ፡ እፍ ፡ ፍሪ ፡ አፍሪካ ፤" (፲፱፻፷) ገጽ ፡ ፻፶፰ ፡ ይመለከቷል፤ "የትዳር ፡ ጓደኝነትን ፡ ማፍረሻ ፡ መሠረታዊ ፡ ዘዬ ፡ ያለው ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ የጋራ ፡ መሆኑ ፡ ሲሆን፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ መበደሉን ፡ ሊያሳይ ፡ ለቻለው ፡ ወገን ፡ ከሌላው ፡ ወገን ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ የተቀነሰ ፤ ካሣ ፡ ይገኛል ።"

ሆኖም ፡ ከእነዚህ ፡ መልሶች ፡ አንዳንዶቹ ፡ በደንብ ፡ የታሰቡና ፡ የተመዛዘኑ ፡ ይመስ ላሉ ። ለምሳሌ ፤ አንድ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙ ፡ ጠበቃ ፡ ጋብቻን ፡ የማፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ ከባድ ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ፤ ምክንያቱም ፡ እንዲህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ "የሴትኛ ፡ አዳሪነት ፡ ይዞታ ፡ (ሙያ) ፡ ሊወገድ ፡ ይችላል ፤ ሕዝቡም ፡ ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ የጋ ብቻን ፡ መፍረስ ፡ በመፈለግ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ዘንድ ፡ ስለማይሄድ ፡ የፍቺው ፡ ቁጥር ፡ ይቀነሳል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሀገሪ ቱን ፡ ይባርካታል ፤" በማለት ፡ የሰነዘሩት ፡ አስተያየት ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ትክክለኛ ነቱ ፡ አጠራጣሪ ፡ ቢሆን ፡ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ አስተሳሰብ ፡ ነው ።

የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ በቀላሉ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችል ፡ ጉዳይ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፡ ካሉት ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ አንደኛው ፡ ሲናገሩ፤ "በእኔ ፡ አስተያየት ፡ የጋብቻ ፡ ዋና ፡ ዓላማው ፡ ተስማምቶ ፡ መኖር ፡ ነው ። ባለትዳሮቹን ፤ በመካከላቸው ፡ ፍቅር ፡ በጠፋች በት ፡ ጊዜ ፡ አብራችሁ ፡ ኑሩ ፡ ብሎ ፡ ማስገደድ ፡ የሕጉን ፡ በኅብረሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ስም ምነት ፡ የመገንባት ፡ ዓላማ ፡ መሳት ፡ ይሆናል ፤" ብለዋል ። ከአንድ ፡ የአሥመራ ፡ አዛ ውንት ፡ የተገኘው ፤ ምናልባትም ፡ ካገኘናቸው ፡ መልሶች ፡ ሁሉ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ የምንለው ፡ አስተያየት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

"ባልና ፡ ሚስት ፡ በጣም ፡ ከመጣመዳቸው ፡ (ከመጠላላታቸው) ፡ የተ ነሳ ፡ የጋብቻቸውን ፡ መፍረስ ፡ እመሻት ፡ (እመፈለግ) ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ከደረሱ ፤ ፍላጐታቸው ፡ እንዲፈጸምላቸው ፡ መፍቀድ ፡ ተገቢ ፡ ይመስለ ኛል ። ሆኖም ፤ ጋብቻን ፡ የማፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ ቀላል ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ብዙ ፡ ባለትዳሮች ፡ በአንዳንድ ፡ ጊዜያዊ ፡ አለመግባባት ፡ ምክንያት ፡ ለመፋታት ፡ ስለሚበቁ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እንደእኔ ፡ ከሆነ ፤ የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ የሚመለከተው ፡ ውሳኔ ፡ የዚያን ፡ የተለየ ፡ ጉዳይ ፡ ግላዊ ፡ ሁኔታ ፡ በመመልከት ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባዋል ፡ እንጅ ፤ በአንድ ፡ በማይነቃነቅ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ሕግ ፡ ሊወሰን ፡ አይገባም ።"

ይህ ፡ አስተያየት ፡ አዲስ ፡ ከሆኑት ፡ "የጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ ለመቀነስ ፡ ከታቀ ዱት ፡ ዘዴዎች ፡ በቀር ፡" በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተጠናቀረውን ፡ ልማዳ ዊውን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ዘዴ ፡ የሚያመለክት ፡ መሆኑን ፡ ማስ ታወስ ፡ ይገባል ።

የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ ከበድ ፡ ሊል ፡ ይገባዋል ፡ ከሚሉትም ፡ መልሶች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከጋብቻ ፡ የሚገኙትን ፡ ሕፃናት ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ። አንድ ፡ በሐረር ፡ የሚገኙ ፡ ጠበቃ ፡ በሰነዘሩት ፡ አስተያየት ፤ በቀላሉ ፡ መፋታት ፡ የሚቻል ፡ ከሆነ ፡ "ለሕፃናት ፡ መልካም ፡ አስተዳደግ ፡ ጥሩ ፡ ቤተሰብ ፡ ማግኘት ፡ ያዳግታል ። ሕፃናት፣ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ ደንበኛ ፡ ጥንቃቄ ፡ ሊደ ረግላቸው ፡ ይገባል ፤" ብለዋል ። በአዲስ ፡ አበባ ፡ በሚገኙት ፡ እጅግ ፡ የበዙ ፡ ደረጃ ፡ አዳሪ ፡ ልጆች ፡ ምክንያት ፡ የተፈጠረውን ፡ ችግር ፡ የተመለከተ ፡ ሁሉ ፤ ለዚህ ፡ አስተ ያየት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።[31] አንድ ፡ በቅርቡ ፡ የተደረገ ፡ ጥናት ፡ እን ዳሳየው ፤ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ከሚገኙት ፡ ሕፃናት ፡ ውስጥ ፡ በፍቺ ፡ ምክንያት፣

31. ደረጀ ፡ ደሬሳ ፤ ስትሪት ፡ ቦይስ ፤ ዘ ፡ ፐሪፊሪያል ፡ ሶሳይቲ ፤ "አዲስ ፡ ሪፖርተር ፤" ሜይ ፡ ፲ ፤ ፲፱፻፷፩ ፤ ገጽ ፡ ፳ ፡ ይመለከቷል ።

ከፈረሱ ፡ ቤተሰቦች ፡ የመጡት ፡ ሕፃናት ፡ በስምምነት ፡ ከሚኖሩ ፡ ቤተሰቦች ፡ ዘንድ ፡ ከመጡት ፡ ሕፃናት ፡ ቁጥር ፡ እጥፍ ፡ ነው ።[32]

የአሥመራው ፡ ብልህ ፡ አዛውንት ፡ የጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ በቀላሉ ፡ ከመፍቀድ ፡ በፊት ፡ ልንመለከታቸው ፡ ይገባል ፡ ከሚሏቸው ፡ "ሁኔታዎች ፡" ውስጥ ፤ ምናልባትም ፡ ከጋብቻው ፡ የተገኙትን ፡ ልጆች ፡ ይዞታ ፡ የሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ አንዱ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ ሳይሉ ፡ አይቀሩም ።

## ክፍል ፡ ሁለት ።

## የጋብቻ ፡ ክርክሮች ፡ አወሳሰን ፤

ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደተመለከተው ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አርቃቂ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የጋብቻ ፡ ክርክሮች ፡ አወሳሰን ፡ እንደ ፤ ኅብረተሰቡ ፡ ፍላጐት ፡ እያደገ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ተስማሚ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ያሰቡትን ፡ ዘዴ ፡ አቅርበዋል ። ይኸኛው ፡ ክፍል ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ በከፍተኛ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ በጊዜው ፡ ባለው ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ያተኩራል ። የሕጉ ፡ አንቀጾች ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ በተለይም ፡ የጊዜው ፡ ልምድ ፡ ሕጉ ፡ የሚሰጣቸውን ፡ መምሪያዎች ፡ ከሚገባው ፡ በላይ ፡ ሲጠቀምባቸው ፡ በሚታይበት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ተጠቅሰዋል ። ሆኖም ፡ ስለጋብቻ ፡ ክርክሮች ፡ አወሳሰን ፡ የሚናገሩትን ፡ ሁሉንም ፡ የሕጉን ፡ አንቀጾች ፡ ለመመልከት ፡ (ለማጥናት) ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሙከራ ፡ አናደርግም ። ለዚህኛው ፡ ጉዳይ ፤ አንባቢው ፡ ቀደም ፡ ባለ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ እትም ፡ ውስጥ ፡ የሰፈረውን ፡ የዊልያም ፡ ቡሐጂያርን ፡ ጽሑፍ ፡ ሊመለከት ፡ ይችላል ።[33]

### የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አጀማመር ፤

በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፤ የጋብቻን ፡ ጉዳይ ፡ ችግሮች ፡ ከሚመለከቱት ፡ በግዴታ ፡ መፈጸም ፡ ካለባቸው ፡ ትእዛዞች ፡ ውስጥ ፡ አንደኛው ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ችግራቸውን ፡ በእነሱ ፡ ለተመረጡ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸው ፡ የሚለው ፡ ነው ።[34] የሕጉ ፡ መንፈስ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹን ፡ ውሳኔ ፡ ትክክለኛነት ፡ ለማጣራትና ፡ ከባድ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉድለቶችም ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔውን ፡ የመለወጥ ፡ መብት ፡ ቢኖራቸውም ፤[35] ጋብቻን ፡ የሚመለከቱ ፡ ክርክሮችን ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የማ

32. ከዶክተር ፡ አር ፡ ዓየል ፡ ጋር ፡ ስለተደረገው ፡ ውይይት ፤ በአዲስ ፡ ሪፖርተር ፤ ግንቦት ፡ ፲፱ ፤ ፲፱፻፷፮ ፤ ገጽ ፡ ፳፪ ፡ ላይ ፡ የተሰጠውን ፡ ሪፖርት ፡ ይመለከቷል ። ለቤተሰቡ ፡ መበተን ፡ ምክንያት ፡ ሊሆኑ ፡ የቻሉት ፡ ሞትና ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ናቸው ።

33. የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፤ ፱ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ፲፱፻፷፮ ፤ ገጽ ፡ ፭፫ ።

34. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ አናቅጽት ፡ ፯፻፳፭ ፡ ፯፻፳፯ ፤ ፯፻፴፩ ።

35. ቢሆንም ፤ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፤ "ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ ከሚደረጉ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነቶች ፤" (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፯፻፴ ፡(፪) የሚነሱትን ፡ ችግሮች ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የመመልከትና ፡ ከጋብቻ ውጭም ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መደረግ ፡ አለመደረጉን ፡ የመወሰን ፡ ኃላፊነት ፡ ተጥሎባቸዋል ፤ ከዚያው ፡ ቁጥር ፡ ፯፻፴/፩ ። በተጨማሪም ፤ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ግንኙነት ፡ "በጋብቻ ፡ የተደረገ ፡ ነው" ፤ ስለዚህም ፡ ችግር ፡ በተነሳ ፡ ጊዜ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ መታየት ፡ ይገባዋል ፤ ወይስ ፡ "ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡" ስለዚህም ፡ ችግር ፡ በተነሳ ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሊታይ ፡ ይገባዋል ፤ ብሎ ፡ የመወሰኑ ፡ ተግባር ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ። ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፯፻፳፬ ። በተጨማሪም ፤ የተፈራ ፡ ባዩንና ፡ ያላዩሽ ፡ ገብሬን ፡ ጉዳይ ፤ (የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፷፫ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፵፯/፷፫) ፡ (ያልታተመ) ፡ ይመለከቷል ።

የት ፡ ሥልጣን ፡ እንደሌላቸው ፡ መደንገግ ፡ ነው ።[36] በተጨማሪም ፤ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ በሚገባ ፡ መስጠት ፡ አለ መስጠታቸውን ፡ የማረጋገጥ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።[37]

ይህ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፤ በጐረቤቶችና ፡ በጓደኞች ፡ አማካይነት ፡ በባልና ፡ ሚስት፡ መካከል ፡ የሚነሱትን ፡ ችግሮች ፡ የማስወገድ ፡ ሙከራ ፡ ቅንጅት ፤ የልማድ ፡ አሰራ ርን ፡ ከማሳየቱ ፡ ሌላ ፤ እንዲሁ ፡ በደፈናው ፡ ሲመለከቱት ፡ ጥሩ ፡ ነገር ፡ ይመስላል ። የጠቅላይ ፡ ን ፡ ነ ፡ ፍ/ቤት ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፤[38] እኒህ ፡ ሰዎች ፡ ባለጉዳዮቹን ፡ በቅ ርብ ፡ ስለሚያውቋቸውና ፡ መሠረታዊ ፡ አቋማቸውንም ፡ አጣርተው ፡ ስለሚያውቁት በአንድ ፡ ወይም ፡ በሁለት ፡ ቀጠሮ ፡ በሚሰሙት ፡ ክርክር ፡ ባለጉዳዮቹን ፡ በማየት ፡ ነገሩን ፡ ከሚወስኑት ፡ ዳኞች ፡ ይልቅ ፡ ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ለመፈለግ ፡ የተሻሉ ፡ ናቸው ።

በአሁኑ ፡ ጊዜ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ ችግሮችን ፡ መፍ ትሔ ፡ መፈለግ ፡ በመሠረቱ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ተግባር ፡ መሆኑን፡ ፍ/ቤቶቹ ፡ ተገንዝበውታል ። ሆኖም ፡ በከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ባለጉዳዮች ፡ በመጀመ ሪያ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚያቀርቡት ፡ የመፋታት ፡ ጥያቄ ፡ እየበረከተ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ነው ! ፍርድ ፡ ቤቶቹም ፤ በማያወላውል ፡ አኳኋን ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ ጥያቄያቸውን ፡ ለቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ከመመለስ ፡ አልቦዘኑም ። ነገር ፡ ግን ፤ ይህ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፋይል ፡ ከመከፈቱም ፡ ሌላ ፤ ብዙ ውን ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔያቸውን ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ መግለጫ ፡ እንዲቀርብለት ፡ መጠየቁ ፡ ሊታወስ ፡ ይገባል ። ስለዚህም፡ ጉዳይ ፤ ማለት ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጉዳያቸውን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚያቀር ቡበት ፡ ምክንያት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ጠበቆቹ ፡ ተጠይቀው ፡ ነበር ። ብዙዎቹ ፡ ምክን ያቱን ፡ ሲያስረዱ ፤ ሕዝቡ ፡ ሕጉን ፡ ስለማያውቀው ፤ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሌሎች ፡ ጉዳዮ ችን ፡ የመመልከት ፡ ሥልጣን ፡ ካለው ፡ የመፋታት ፡ ጥያቄዎችንም ፡ ይመለከታል ፡ ብሎ ፡ ስለሚያምን ፡ ነው ፡ ብለዋል ። በርከት ፡ ያሉት ፡ ደግሞ ፤ ይህ ፡ ልምድ ፡ ለሁ ለት ፡ ምክንያታዊ ፡ ጥቅሞች ፡ ሲባል ፤ በማወቅ ፡ ሆነ ፡ ተብሎ ፡ የሚደረግ ፡ ነው፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ሰንዝረዋል ።

አንደኛው ፤ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ከሰፈራቸው ፡ ውስጥ ፡ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞችን ፡ በሚመርጡበት ፡ ጊዜ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ የሥልጣን ፡ ድጋፍ ፡ ማግኘት ፡ ነው ። የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ከከተማዎች ፡ መቆርቆር ፡ በፊት ፡ ከገ ጠሬው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፡ የተገኘ ፡ በደንብ ፡ የተደራጀ ፡ ልማድ ፡ ነው ። በዚያ ፡ (በገጠሬው) ፡ አካባቢ ፡ የኅብረተሰቡ ፡ የወደፊት ፡ ዕድል ፡ በቅርብ ፡ የተሳሰረ ፡ ነው ። ቤተዘመድ ፤ ጓደኞችም ፡ ሆኑ ፡ የሰፈሩ ፡ አዛውንት ፡ ለሽምግልና ፡ በተጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃደኞች ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ሳይጠየቁም ፡ ለማስታረቅ፡ ይሞክራሉ ። ሆኖም ፡ ከየቦታቸው ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ በበዙበትና ፡ ራስን ፡ ችሎ ፡ ከብዙ ሰው ፡ ጋር ፡ ሳይገናኙ ፡ የመኖር ፡ ስሜት ፡ በሰፈነበት ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ በመሆን ፡ ያለምንም ፡ የድካም ፡ ዋጋ ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ለመ

36. ከዚያው ፤ ቁጥር ፡ ፯፻፴፯ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቍጥሮች ፡ ፫፻፲፱/፩ ፤ ፫፻፶—፫፻፶፩።
37. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፯፻፳፱ ።
38. የሰይፉ ፡ የተሻወርቅና ፡ የበላዩ ፡ ታደሰ ፡ ጉዳይ ፤ (የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፷ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፸፬/፷) ፡ (ያልታተመ) ።

ሥራት ፡ የሚፈልጉ ፡ ወዳጆች ፡ ማፍራት ፡ በመጠኑ ፡ የሚያዳግት ፡ ነው ።[39] በዚህም ፡ ምክንያት ፤ ብዙዎች ፡ ባለትዳሮች ፡ የመረጧቸው ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ጉዳያቸውን፡ ማየት ፡ ይችሉ ፡ ዘንድ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ "ትእዛዝ" ፡ ለማግኘት ፡ ይጥራሉ ። ይህም ፤ ምናልባት ፡ ፈቃደኛ ፡ ባልሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሥልጣን ፡ ፍራቻን ፡ ያሳድርባቸዋል።[40]

መጀመሪያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመሄድ ፡ ይገኛል ፡ የሚባለው ፡ ሌላው ፡ ጥቅም ፡ ደግሞ ፡ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የጋብቻቸውን ፡ መፍረስ ፡ በፈቀዱ ፡ ጊዜ ፤ የንብረትን ፡ ክፍያና ፡ የሕፃናትን ፡ አስተዳደግ ፡ ሁኔታ ፡ በሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ የሚሰጡትን ፡ ውሳኔ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ የማስፈጸምን ፡ ዋስትና ፡ ለማግኘት ፡ በማሰብ ፡ ነው ።[41] የተፈረደበት ፡ ወገን ፡ እንቢተኛ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፤ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አስገዳጅነት ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሊያገኝ ፡ ይችላል ።[42] ስለዚህም ፡ ከግልግሉ ፡ ዳኝነት ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ መሄድ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፤ ይህን ፡ ልዩነት ፡ የተገነዘቡት ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። አንድ ፡ ጠበቃ ፤ ብዙዎቹን ፡ ደንበኞቻቸውን ፡ በተለይም ፡ ሴቶቹን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ ጉዳያቸውን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ እንዲያዩላቸውና ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የሽማግሌዎቹን ፡ ውሳኔ ፡ "ያጸድቅላቸው" ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲሄዱ ፡ ሲመክሯቸው ፤ ብዙዎቹ ፡ ደንበኞቻቸው ፡ ግን ፡ መጀመሪያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መሄድን ፡ የሚመርጡ ፡ መሆናቸውን ፡ ገልጸውልናል ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ የባለጉዳዮቹ ፡ በመጀመሪያ ፡ ከፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ መቅረብ ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ውጤት ፡ ማስገኘቱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የጀመሩት ፤ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አካባቢ ፡ ከሚገኙ ፡ ጠበቆች ፤ የሕዝብ ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊዎች ፤ ሕግ ፡ አዋቂዎችና ፡ ከተማሩ ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ የተመረጠ ፡ "ሰብሳቢ ፡ ዳኛ" የመሾም ፡ ልምድ ፡ ነው ። ይህ ፡ ልማድ ፤ የሕጉን ፡ መምሪያዎች ፡ የተከተለ ፡ ሥርዓታዊ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ እንዲኖር ፡ ከማበረታታቱም ፡ በላይ ፡ የማ

---

39. በደቡብ ፡ ናይጀሪያ ፡ ያለውን ፤ በኢትዮጵያ ፡ ካለው ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰለውን ፤ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ቅንጅት ፡ ያወዳድሯል ፤ "አብዛኛው ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጠው ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ነው ፤ ---ይሽም ፡ ከፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውጭ ፡ የሚሰጠው ፡ የማፋታት ፡ ውሳኔ ፡ ከእንግዲህ ፡ ሕጋዊ ፡ አይደለም ፤ ማለት ፡ አይደለም ፡ የዚህ ፡ ትርጉም ፡ በቀላሉ ፤ በሕብረተ ፡ ሰቡ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ግላዊ ፡ መሆን ፡ እየቀረ ፡ ሲሄድ ፤ ምንም ፡ ያህል ፡ (የጥሎሽ ፡ ገንዘብ ፡) ተከፍሏል ፡ አልተከፈለም ፤ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ ለቆየ ፡ ጋብቻ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መከፈል ፡ ይገባዋል ፡ የሚለውን ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጅ ፡ ጉዳይ፡ ለመመልከት ፡ ፈቃደኛ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ቁጥር ፡ እያነሰ ፡ ሲሄድ ፤ እንነዚህን ፡ መሰል ፡ ጉዳዮች ፡ ሥራዬ ፡ ብለው ፡ በያዙት ፡ ዳኞች ፡ አማካይነት ፡ በፍርድ ፡ መታየቱ ፡ በጉዳዩ ፡ ውስጥ ፡ ላሉ ፡ ሁሉ ፡ በይበልጥ ፡ የሚስማማ ፡ ይሆናል ። "ኤስ ፡ ቸንውቢ ፡ አቢ ፤" ዘመናዊ ፡ የቤተሰብ ፡ ሕግ ፡ በደቡብ ፡ ናይጀሪያ ፤ (በእንግሊዝኛ) ፡ የተጻፈ ፡ (፲፱፻፶፰) ፤ ገጽ ፡ ፫፻፭ ።

40. በተጨማሪም ፤ የምልኬ ፡ ጉርሙንና ፡ የናዴሳ ፡ በዳዳን ፡ ጉዳይ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፷ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰/፷) ፡ (ያልታተመ) ይመለከቷል ። በዚህም ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፤ ባልየውን ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ በተከታታይ ፡ አልቀረበም ፡ በማለት ፡ ያስቸግር ፡ እንበረበት ፤ ቀደም ፡ ብሎ ፡ የተመረጡ ፡ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ፊት ፡ እንዲቀርብ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አዟል።

41. ለምሳሌም ፤ የመጋቢት ፡ ፰/፲፱፻፶፯ ፤ ውሳኔ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ጂማ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯/፶፯) ፡ (ያልታተመ) ፡ የቀድሞው ፡ ባል ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ለቀድሞ ፡ ሚስቱ ፡ እንዲሰጥ ፡ የበየኑበትን ፡ ፪፻፶ ፡ የኢት ፡ ብር ፡ ለመክፈል ፡ ባለመፍቀዱ ፡ ስድስት ፡ ወር፡ ታስሯል) ። የአበራ ፡ ጠበየና ፡ የየማንሽ ፡ ዓለሙ ፡ ጉዳይ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፷ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፵፩/፷) ፡ (ያልታተመ) ፡ (የቀድሞው ፡ ባል ፡ አሠሪ/ቀጣሪ ለቀድሞዋ ፡ ሚስት ፡ የሚገባትን ፡ ገንዘብ ፡ ከባልየው ፡ ሂሳብ ፡ ላይ ፡ እየቀነሰ ፡ እንዲሰጥ፡ ታዟል)። የጥሩነሽ ፡ ተክለ ፡ ብርሃን ፡ የገብሬ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ ጉዳይ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፶፯ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፸፰/፶፯ ) ፡ (ያልታተመ) ፡ (እንደዚያው) ።

42. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፫፻፲፱ /፪ ።

ፋታቱ ፡ ውሳኔም ፡ በጽሑፍ ፡ እንዲሆን ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳል ። ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፤ ሰብሳቢውን ፡ ዳኛ ፡ ስለውሳኔው ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ስለሚጠይቁም ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተሟላ ፡ ባይሆን ፤ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለጋብቻ፡ መፍረስ ፡ አንድ ፡ መዝገብ ፡ ለማቆየት ፡ ይቻላል ።[43]

ሰብሳቢ ፡ ዳኛን ፡ የመሾምና ፡ የሽምግልናውን ፡ ዳኝነት ፡ አፈፃጸም ፡ ዝርዝር ፡ መግለጫ ፡ በመጠየቅ ፡ ረገድ ፡ ለሚደረገው ፡ የቁጥጥር ፡ ልምድ ፡ በሕጎቹ ፡ ውስጥ ፡ ድጋፍ ፡ ማግኘት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ።[44] ክርክሩን ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች፡ ካዩት ፡ በኋላ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በተጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ በነገሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ እንዲመረምርና ፡ ውሳኔውን ፡ እንዲያጸድቅ ፡ የሚያስችለው ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የሚገኘው፡ ሥልጣን ፡ በአሰራር ፡ በኩል ፡ ትክክለኛ ፡ ላይሆን ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ ሕጉ ፡ ይህን ፡ አስፈላጊ ፡ የትርጉም ፡ ልዩነት ፡ ለመጨመር ፡ የሚችል ፡ ይመስላል ። ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ሕጉ ፡ ሊሻሻል ፡ ይገባዋል ።

ይህ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አማካይነት ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኞችን ፡ የመሾም ፡ ልምድ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ ቢሆንም ፤ ይኸው ፡ ልምድ ፡ ለሰብሳቢ ፡ ዳኞቹ ፡ ችግርን ፡ ፈጥሯል ። የሰዎቹ ፡ አሿሿም ፡ የተወሰነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የለውም ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ በዚያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አካባቢ ፡ የሚያውቁት ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ ጉዳይ፡ ጸሐፊ ፡ እንዳለ ፡ ይጠየቃሉ ። የሚያውቁት ፡ ካለ ፤ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ይሾማል ። ከሌለም ፤ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ተስማሚ ፡ ነው ፡ የተባለ ፡ በቅርብ ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፡ ይመረጣል ። ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ለድካሙ ፡ ዋጋ ፡ የሚከፈለው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ። በተጨማሪም ፤ ይኸ ፡ ቅጥ ፡ ያጣ ፡ የአመራረጥ ፡ ዘዴ ፤ ዳኛው ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ለሚመለከተው ፡ ሰው ፡ የማይገባ ፡ ሸክም ፡ ሊሆንበት ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ጠበቃ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ሰብሳቢ ፡ በመሆን ፡ ያበረከቱትን ፡ አገልግሎትና ፡ ይህም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ በኩራት ፡ ካወጉን ፡ በኋላ ፤ በቅርቡ ፡ በስምንት ፡ የሽምግልና ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ በመሆን ፡ ባገለገሉበት፡ ወቅት ፤ ጥቅም ፡ ሊያስገኝላቸው ፡ ለሚችለው ፡ ሥራቸው ፡ ሊያውሉት ፡ የቻሉት ፡

---

43. ከሬጅስትራሩ ፡ መረዳት ፡ እንደተቻለው ፤ በ፲፱፻፸ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተመዘገቡትን ፡ የመፋታት ፡ ብይኖች ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፷፫ ፡ ደርሷል ። ዘ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሄራልድ ፤ ግንቦት ፡ ፳፯ ፤ ፲፱፻፸፮ ፤ ገጽ ፡ ፯ ፤ ፫ኛው ፡ ዓምድ ።

44. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ አንቀጽ ፡ ፫፻፲፮/፪ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይደነግጋል ፤ "የግልግል፡ ዳኛ ፡ ወይም ፡ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ጉባኤ ፡ አባል ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲመረጥ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፤ ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለጉዳዩ ፡ ተስማሚ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ መርጦ ፡ ሊሾም ፡ ይችላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ሽማግሌዎች ፡ እንዲመርጥ ፡ ታዞ ፡ እንቢ ፡ ካላለ ፡ ወይም ፤ የተመረጠው ፡ ሰው ፡ የሽምግልናውን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ፈቃደኛ ፡ ካልሆነ ፤ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥሮች ፡ ፴፫፻፴፩/፪ ፤ ፴፫፻፴፭) ፡ ወይም ፤ ሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ በመስማማት ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ መምረጥ፡ ያለባቸው ፡ ሲሆንና ፡ በተባለው ፡ ምርጫ ፡ ያልተስማሙ ፤ (ከዚያው ፤ አንቀጽ ፡ ፴፫፻፴፬) ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ በተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ ሽማግሌዎቹን ፡ እንዲመርጡ ፡ አይገደዱም ፡ ይህ ፡ በመጨረሻ ፡ የተጠቀሰው ፡ አንቀጽ ፡ (፴፫፻፴፬) ፡ ምናልባት ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛን ፡ ለመሾም ፡ የሚያስችል ፡ ሥልጣን፡ ይሰጥ ፡ ይሆናል ፤ ቢሆንም ፤ ሳያቋርጥ ፡ የሚደረገው ፡ ቁጥጥር ፡ በሕጉ ፡ ያልተደገፈ ፡ ነው ። የሰይፉ ፡ የተሻወርቅንና ፡ የበልዩ ፡ ታደሰን ፡ ጉዳይ ፤ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፷ ፤ የፍትሐ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፸፩/፷) ፡ (ያልታተመ) ፡ ይመለከቷል ። በዚህም ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤት፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሥልጣን ፡ ሕጋዊ ፡ መሠረት ፡ ተከራክረውበት ፡ ነበር ። ዳኑ ፡ ግን ፤ ቀጥተኛ ፡ መልስ ፡ ሳይሰጥበት ፡ ቀርቷል ። በተጨማሪም ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ መድከማቸውንና ፡ ተስፋ ፡ መቁረጣቸውን ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ጉዳዩን ፡ በማየት ፡ ረገድ ፡ ለመቀጠል ፡ አለመፈለጋቸውን ፡ ቢገልጹም ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ እንደገና ፡ እንዲመረምሩ፡ ሽማግሎቹን ፡ ያዘዘበትን ፡ የአሰለፈች ፡ መኰንንና ፡ የአምሀ ፡ አበራን ፡ ጉዳይ ፤ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፷ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፻፸፩/፷) ፡ (ያልታተመ) ፡ ይመለከቷል ።

ጊዜ ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ እጅግ ፡ ማጠሩን ፡ ገልጸዋል ።[45] በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ያልተመረጡ ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች፡ ያገለገሉ ፡ ጠበቆች ፡ ተገኝተዋል ። አመራረጡን ፡ ርቱዕ ፡ ለማድረግ ፡ ከሁለት ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ መፈጸም ፡ ሳይቻል ፡ አይቀርም ። ይኸውም ፤ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለተሰማሩት ፡ ሁሉ ፡ ሥራውን ፡ በትክክል ፡ ለማከፋፈል ፡ የሚያስችል ፡ ዘዴ ፡ መፍጠር ፤ ወይም ፡ ተሿሚዎቹ ፡ ለዚህ ፡ ተግባር ፡ ለሚያጠፉት ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ መመደብ ፡ ናቸው ።[46]

የፍቺ ፡ መጠየቂያ ፡ ለማቅረብ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ተመራጭነት ፡ አላቸው ።[47] በተጨማሪም ፤ ለወረዳ ፡ ወይም ፡ አንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችና ፡ ለከፍተኛው ፡ (ሦስተኛ ፡ ደረጃ) ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ማመልከቻዎች ፡ እንደሚቀርቡ ፡ ተደርሶበታል ።[48] ከፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰ ፡ ለመረዳት ፡ እንደምንችለው ፤ የጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ ጉዳይ ፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፡ ለመመልከት ፡ የሚችሉት ፡ አውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ። አንቀጹ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤ "በገንዘብ ፡ ግምት ፡ ሊወሰን ፡ በማይችል ፡ ሀብት ፡ ምክንያት ፡ የሚቀርብ ፡ ክስ ፡ የሚታየው ፡ ክሱ ፡ በተነሳበት ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ።" ባለሥልጣኖች ፤ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ጉዳይ ፤ ክብርን ፡ የሚመለከት ፡ ረቂቅ ፡ ጉዳይ ፡ በመሆኑ ፡ በገንዘብ ፡ ግምት ፡ ሊወሰን ፡ የማይችል ፡ ስለሆነ ፤ ይህን ፡ አንቀጽ ፡ የጋብቻ መፍረስ ፡ ጥያቄዎችንም ፡[49] እንደሚጨምር ፡ አድርገው ፡ ተርጉመውታል ። ነገር ፡ ግን ፤ በቅርቡ ፡ የተሰጠ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ በዚህ ፡ ትርጉም ፡ የተስማማ ፡ አይመስልም ።[50] በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የመፋታት ፡ ጥያቄ ፡ ማመልከቻ ፡ ቀርቦለት ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ሰብሳቢ ፡ ከሾመ ፡ በኋላ ፤ እራሱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተቆጣጣሪነት ፡ ተግባር ፡ ለማከናወን ፡ ወሰነ ። ከባለጉዳዮቹ ፡ አንደኛው ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ን ፡ ጠቅሶ ፤ ጉዳዩ ፡ ለአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ ይገባዋል ፡ በማለት ፡ ተቃወመ ። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ ተቃዋሚውን ፡ ወገን ፡ እንደማይደግፈው ፡ በደፈናው ፡ ገልጾ ፤ ጉዳዩ ፡ በይግባኝ ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ጸድቋል ። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ ለአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ነገሮችን ፡ የማየት ፡ ሥልጣን፡

45. በተጨማሪም ፤ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ በሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ ሆኖ ፡ በማገልገል ፡ ላይ ፡ መሆኑን ፤ የማታ ፡ ትምህርት ፡ የሚማር ፡ መሆኑንና ፡ ፕሮግራሙም ፡ በጣም ፡ የሚማታበት ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽ ፡ የሰብሳቢ ፡ ዳኝነት ፡ ሥራውን ፡ ያስወገደበትን ፡ የሊሻን ፡ በላይንና ፡ የከተማ ፡ ይልማን ፡ ጉዳይ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፶፯ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፭/፶፭)፡ (ያልታተመ) ፡ ይመለከቷል ።

46. ከተከበሩ ፡ አቶ ፡ አሰፋ ፡ ሊበን ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዴንት ፤ ጋር ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፱/፲፱፻፷፩ ፤ የተደረገ ፡ ውይይት ።

47. ለምሳሌም ፤ የአበራ ፡ ጠበየና ፡ የየማነሽ ፡ ዓለሙ ፡ ጉዳይ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፷ ፤ የፍትሐ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፵፩/፷) ፡ (ያልታተመ) ፡ ጉዳዩ ፡ ከአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ እዚህ ፡ የመጣ ፡ ነበር ።

48. ለምሳሌም ፤ የብርሃኑ ፡ ሃብተየስና ፡ የአዛለች ፡ ክንፋ ፡ ጉዳይ ፤ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ነገሥት ፍርድ ፡ ቤት፤ ፲፱፻፶፱ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፴፪/፶፱) ፡ (ያልታተመ) ፡ ጉዳዩ ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ የመጣ ፡ ነበር ።

49. አር ፡ ሴድለር ፤ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ (በእንግሊዝኛ ፡ የተጻፈ) ፤ ፲፱፻፷ ፤ ገጽ ፡ ፳፰ ።

50. የበላይነሽ ፡ አወቀና ፡ የነጋ ፡ ፋንታ ፡ ጉዳይ ፤ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት፤ ፲፱፻፶፱ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥጥር ፡ ፩፻፸፪/፷) ፡ (ያልታተመ) ።

የሚሰጠው ፤ የሀብቱ ፡ መጠን ፡ ልክ ፡ ከክርክር ፡ በፊት ፡ በትክክል ፡ በገንዘብ ፡ ሊገመት ፡ የማይችል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የተረጐመው ፡ ይመስላል ። የአንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ አርቃቂ ፡ ያሰቡት ፡ ይህ ፡ ቢሆንም ፡ ባይሆንም ፤ በኢትዮጵያዊው ፡ ቅንጅት ፡ ውስጥ ፡ የልዩ ፡ ልዩዎቹ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ በመሠረቱ ፡ የሚወሰነው ፡ በጉዳዩ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ የገንዘብ ፡ ልክ ፡ በመሆኑና ፤ መጠኑም ፡ ከክርክሩ ፡ በፊት ፡ በገንዘብ ፡ ግምት ፡ ሊወሰን ፡ በማይቻልበት ፡ ጊዜ ፡ ጉዳዩ ፡ ለመካከለኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፤ ማለትም ፡ ለአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚቀርብ ፡ በመሆኑ ፤ ይህ ፡ አተረጓጐም ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሀተታውን ፡ በማራዘም ፤ ጉዳዩ ፡ መጠኑ ፡ ያልተገለጸ ፡ የንብረት ፡ ክፍያን ፡ የሚመለከት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ የጋብቻ ፡ መፍረስንም ፡ ሁኔታ ፡ የሚጠቅስ ፡ በመሆኑ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መቅረብ ፡ ይችላል ፡ ብሏል ። ይህ ፡ በመጨረሻ ፡ የተገለጸው ፡ ሃሳብ ፡ ስሕተት ፡ ይመስለናል ፤ ምክንያቱም ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ መሠረት ፡ መጠኑ ፡ ያልተወሰነ ፡ የገንዘብ ፡ ክርክር ፡ ካለባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ይልቅ ፤ የጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ ሁኔታ ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ለአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የተሰጠ ፡ ስለሚመስል ፡ ነው ።

የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነትን ፡ ሥራ ፡ በመቆጣጠር ፡ ረገድ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እኩል ፡ የሆነ ፡ ችሎታ ፡ እንዳላቸው ፡ የታየ ፡ ስለሆነ ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ የተቆጣጣሪነት ፡ ተግባር፡ በመውሰድ ፡ በሕጉ ፡ የታቀደውን ፡ የሥራ ፡ ድልድል ፡ ማወዛገቡ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ አይታይም ። በተጨማሪም ፤ ይህን ፡ ሥራ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ጠቅልለው ፡ እንዲያከናውኑት ፡ ቢደረግ ፤ ሥራው ፡ ለሦስቱ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከተከፋፈለበት ፡ ከአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ የሥራ ፡ ቅልጥፍናና ፡ ልምድ ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል ።[51]

## ስለቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ አሠራር ፤

### የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ አመራረጥ ፤

ባለጉዳዮቹ ፡ በመጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሄዱ ፡ እንደሆነ ፡ ወደ ፡ ቀበሌያቸው/ሰፈራቸው ፡ ተመልሰው ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፤ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ እንዲመርጡ ፡ ይነገራቸዋል ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያልሄዱ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ምርጫ ፡ ችግራቸውን ፡ ለማስወገድ ፡ የመጀመሪያው ፡ እርምጃ ፡ ይሆናል ። ባልየውና ፡ ሚስትየዋ ፡ ወይም ፡ የእያንዳንዳቸው ፡ የቅርብ ፡ ዘመዶች ፤ እያንዳንዱን ፡ ወገን ፡ የሚወክሉትን ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ እኩል ፡ በእኩል ፡ ይመርጣሉ ።[52] አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ የሽማግሌዎቹን ፡ ቁጥር ፡ ጐደሎ ፡ ለማድረግ ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፡ ገለልተኛ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በባለጉዳዮቹ ፡ ወይም ፡ በዘመዶቻቸው ፡ ይመረጣል ።[53] በገለልተኛው ፡ ሰው ፡ አመራረጥ ፡

---

51. በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሁሉንም ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ጉዳዮች ፡ የማይለዋወጡ ፡ ሁለት ፡ ዳኞች ፡ እንዲመለከታቸው ፡ ማድረጉ ፡ ወደ ፡ ትክክለኛው ፡ እርምጃ ፡ ነው ። ከተከበሩ ፡ አቶ ፡ ንጉሤ ፡ ፍትሕ ፡ አወቅ ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፤ ጋር ፡ ሰኔ ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፤ ፲፱፻፷፩ ፤ የተደረገ ፡ ውይይት ።

52. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥሮች ፡ ፯፻፳፭ ፤ ፯፻፴፭ ፡ ይመለከቷል ።

53. አንደኛው ፡ ወገን ፡ ለመምረጥ ፡ ካልፈቀደ ፤ ወይም ፡ ካልቻለ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ምርጫውን ፡ እንዲያከናውን ፡ መጠየቅ ፡ ይቻላል ። ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፶፪ን ፡ ይመለከቷል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ሳልተገኘው ፡ ወገን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ እንዳይሾም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተወስኗል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፤ አግባብነት ፡ ያለው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ራሱ ፡ ጉዳዩን ፡ ተመልክቶ ፡ መወሰን ፡ ነው ። የፎርቲና ፡ የፎርቲ ፡ ጉዳይ ፡ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፶፯) ፡ <u>የኢት ፡ ሕግ ፡</u>

ላይ ፡ ያልተስማሙም ፡ እንደሆነ ፤ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ የተመረጡት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ገለልተኛውን ፡ ሰው ፡ እንዲመርጡ ፡ ይደረጋል ።[54]

ለጥናታችን ፡ በቀረቡት ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ የተዘወተረው ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች፡ ቁጥር ፡ አምስት ፡ ሲሆን ፤[55] ሦስት ፡ አራትና ፡ ስድስት ፡ ሰዎች ፡ የተካፈሉባቸው ፡ ነገሮች ፡ ደግሞ ፡ የሚቀጥለውን ፡ ደረጃ ፡ ይዘዋል ። በሁለት ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ስምንት ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ሲገኙ ፤ በአንደኛው ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ተመርጧል ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከተቆጣጠራቸው ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነቶች ፡ ውስጥ ፡ እጅግ የበዛው ፡ ክፍል ፡ (በመቶ ፡ ሰማንያ ፡ ስምንቱ)፡ አምስት ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የነበሩባቸው ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በሁለት ፡ ባለትዳር ፡ መካከል ፡ አለመግባባት ፡ መኖሩን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፤ ሽማግሌዎቹ ፡ (ጉዳዩን ፡ ለመስማት) ፡ እራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ይሾማሉ ። እነዚህ ፡ ጉዳዮች ፡ በሚሰሙ ፡ ጊዜ ፡ መጨጨህ ፡ እጅግ ፡ የበዛባቸው ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ሲናገሩ ፤ ከሁለት ፡ ባለትዳር ፡ ቤት ፡ የሚመነጨው ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ የማያቋርጥ ፡ ጭቅጭቅና ፡ ጩኸት ፡ እሳቸውና ፡ ሌሎችም ፡ እጅግ ፡ ስለመረራቸው ፤ እራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ጉዳዩ ፡ ውስጥ ፡ በማስገባት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ መጀመራቸውን ፡ አስረድተዋል ።[56]

ለዓይነት ፡ ከቀረቡልን ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ማዕከላዊ ፡ እድሜ ፡ ፵፩ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ከ፳፫ ፡ እስከ ፡ ፸ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ለሽምግልና ፡ ሲመረጡ ፤ በርካታዎቹ ፡ በ፴፫ና ፡ በ፵፭ ፡ ዓመት ፡ የእድሜ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው ። ለሥራው ፡ በጣም ፡ ወጣት ፡ በመሆን ፡ ለሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ተመርጬ ፡ አላውቅም ፡ ካለው ፤ በመጀመሪያ ፡ የ፳ ፡ ዓመት ፡ እድሜ ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ እንደተረዳነው ፤ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ በእድሜ ፡ ገፉ ፤ በብልህነታቸው ፡ ላቅ ፡ ያሉት ፡ የኅብረ ፡ ሰብ ፡ አባሎች ፡ ተግባር ፡ ነው ።

በጐረቤቶች ፤ በዘመዶችና ፡ በጓደኞች ፡ የተደረጉ ፡ ውክልናዎች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲነጣጠሩ ፤ የተመዛዘኑ ፡ ናቸው ፤ ይኸውም ፡ እንደቅደም ፡ ተከተላቸው ፡ በ፩፻፵፯ ፤ ፩፻፴፯ና ፡ ፩፻፯ ፡ ሰዎች ፡ ተከናውነዋል ። ከቃል ፡ ተጠያቂዎቹ ፡ ግምት ፡ ለመረዳት ፡ እንደተቻለው ፤ በጓደኝነትና ፡ በጉርብትና ፡ መልክ ፡ የተወከሉት ፡ ሽማግሌዎች ፤ ባለጉዳዮቹን ፡ በማወቅ ፡ ረገድ ፡ ያላቸው ፡ ማዕከላዊ ፡ ጊዜ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ይሆናል ። ጋብቻው ፡ "የነገር ፡ አባቶች ፡"[57] ወይም ፡ ምስክሮች ፡ ያሉት ፡ ከሆነ ፤ እኒህ፡ ሰዎች ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ለሽምግልናው ፡ ተግባር ፡ ይመረጣሉ ።

---

መጽሔት ፤ ፩ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ገጽ ፡ ፳፰ ። ዳግም ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ተመራጮቹ ፡ ጋብቻው ፡ ሲፈጸም ፡ ምስክሮች ፡ ቢሆኑም ፤ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ካልፈቀደ ፡ በስተቀር ፤ ሌላው ፡ ወገን ፡ ብቻውን ፡ ሁሉንም ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ መምረጥ ፡ አለመቻሉ ፡ ተወስኖአል ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ከተደረገ ፡ በግልግል ፡ ዳኝነት ፡ የተሰጠ ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ። የትልቅ ፡ ሰው ፡ ቦጋለና ፡ የተረጩ ፡ ሽፈራው ፡ ጉዳይ ፤ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፳፰ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፴፱/፶) ፡ (ያልታተመ ፡)

54. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፯፻፴፩ ፡ ይመለከቷል ።

55. ማዕከላዊው ፡ ቁጥር ፡ 4.8

56. በአንድ ፡ በወሰጋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በተነሳ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፤ ከሁለት ፡ ሚስቶች ፡ ውስጥ ፡ በእድሜ ፡ ወጣት ፡ የሆነችው ፤ በባልዋና ፡ በመጀመሪያ ፡ ሚስቱ ፡ መካከል ፡ የተፈጠረውን ፡ ችግር ፡ ለማስወገድ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹን ፡ የመምረጡን ፡ ተግባር ፡ እራሷ ፡ ከመውሰድዋ ፡ በላይ ፤ እራሷን በራሷ ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ በማድረግ ፡ ጠበኞቹን ፡—እግዜር ፡ ይባርካትና ፡—ለማስታረቅ ፡ ችላለች ።

57. የጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ ችግር ፡ በተፈጠረ ፡ ጊዜ ፤ ባለትዳሮቹ ፡ ሄደው ፡ ምክርን ፡ የሚጠይቋቸው ፡ እንደቋሚ፡ አማካሪ ፡ ሆነው ፡ የሚያገለግሉ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ የቅርብ ፡ ጓደኞች ፤ ወይም ፡ የሩቅ ፡ ዘመዶች፡ እንዲኖሩ ፡ ማድረግ ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የሸዋ ፡ ልዑል ፡ ኃይለ ፡ ማርያምንና ፡ የደበበ ፡ ኃይሌን ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከቷል ።

ለዓይነት ፡ ካጠናናቸው ፡ ፭፻፳ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ፡ ብቻ ፡ ተገኝተዋል ።[58] ይህንን ፡ ያጋደለ ፡ ሁኔታ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ የተረዱ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፤ የሽምግልናው ፡ ጓድ ፡ ወንዶች ፡ ብቻ ፡ የሚገኙበት ፡ ስለሆነ ፤ የሴቲቱን ፡ ችግር ፡ በቅጡ ፡ ለመረዳት ፡ ያዳግታል ፤ ይህም ፡ በመሆኑ ፡ የሴቲቱ ፡ ወገን ፡ እንደሚ በደል ፡ ገልጸዋል ። እንዲሁም ፡ ሆኖ ፡ ኢትዮጵያውያት ፡ ሴቶች ፡ ሃሳባቸውን ፡ ለቤተ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የሚያስረዱበትን ፡ ዘዴ ፡ ፈጥረዋል ። የሴት ፡ ምስክሮ ችና ፡ ተመልካቾች ፤ በተለይም ፡ የባልና ፡ ሚስቱ ፡ እናቶች ፡ በሽምግልናው ፡ ጉባኤ ፡ ወቅት ፡ ተሰሚነት ፡ ያላቸው ፡ ተካፋዮች ፡ ናቸው ።

የሚያከራክር ፡ ቢሆንም ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕጉ ፤ የቤተዘመድ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ሹመታቸውን ፡ መቀበል ፡ ወይም ፡ አለመቀበላቸውን ፡ በጽሑፍ፡ እንዲያረጋግጡ ፡ ይፈቅዳል ። ነገር ፡ ግን ፤ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ የሽም ግልና ፡ ዳኝነት ፡ ውስጥ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ስላለውና ፤ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ለሚሾሙ ፡ የሽም ግልና ፡ ዳኞች ፡ የተወሰነ ፡ ሊሆን ፡ ስለሚችል ፤ ተፈጻሚነቱ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ።[59] የመሃይምናን ፡ ብዛት ፡ ከፍተኛ ፡ በሆነበት ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ በአሰራር፡ በኩል ፡ እምብዛም ፡ ትርጉም ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ ለተደረጉ ፤ ማለትም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ በሾመባ ቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ለሽምግልናው ፡ ጓድ ፡ በጠቅላላው ፡ ሹመቱን ፡ መቀበል ፡ አለመቀበላቸውን ፡ በመግለጽ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በጽሑፍ ፡ ከሚ ያመለክተው ፡ በስተቀር ፤ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ የጽሑፍ ፡ መልሶች ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ (፲፮ ፡ በመቶ) ፡ የሚሰጡ ፡ ናቸው ።

## የሽምግልናው ፡ ጉባኤ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፤

ለሽምግልና ፡ ጉባኤ ፡ እጅግ ፡ የተለመደው ፡ (በመቶ ፡ ሃምሳ ፡ በሚሆነው) ፡ ቦታ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጽር ፡ ግቢ ፡ ሲሆን ፡ ጊዜው ፡ ደግሞ ፡ እሁድ ፡ ጠዋት ፡ ነው ። ለጥቀውም ፤ እንደተዘውታሪነት ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፤ የባለትዳሩ ፡ ቤት ፤ ከሽማግሌዎቹ፡ የአንዱ ፡ ቤት ፤ ከባለትዳሩ ፡ ዘመዶች ፡ የአንደኛው ፡ ቤት ፤ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ቅጽር ፡ ግቢና ፡ ገላጣ ፡ መስክ ፡ የተለመዱ ፡ የሽምግልና ፡ ጉባኤ ፡ ቦታዎች ፡ ናቸው ። አንድ ፡ ላላ ፡ ያለ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ በቡና ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተደርጓል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ትክክል ፡ የሆነ ፡ የቁጥር ፡ ማስረጃ ፡ ባይኖርም ፤ ከቤተክርስቲያን ፡ ቅጽር ፡ ግቢ ፡ ውጭ ፡ ከተደረጉት ፡ የሽምግልና ፡ ጉባኤዎች ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞቹ ፡ ምናልባት ፡ ክርስ ቲያን ፡ ያልሆኑ ፡ ሰዎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ሳይሆኑ ፡ አልቀሩም ።

እሑድ ፡ ጠዋት ፡ ከቅዳሴው ፡ መልስ ፤ የሽምግልና ፡ ጉባኤው ፡ ተካፋዮች ፡ ከሌ ሎች ፡ ተመሳሳይ ፡ ስብሰባዎች ፡ በተራራቀ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ይሰበሰባሉ ። አንዳንዴ ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ እስኪጠሩ ፡ ድረስ ፡ ከሽማግሌዎቹ ፡ ተነጥለው ፡ እንዲቀመጡ ፡ ይደ ረጋል ። ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፤ ሁሉም ፡ ተካፋዮች ፡ አብረው ፡ ይቀመጣሉ ፡ ወይም ፡ ይቆማሉ ። ባጠናናቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ቤተዘመዶችና ፡ ጓደኞች ፡ አንዳንዴ ፡ (ከነገሮቹ ፡ በመቶ ፡ ሃያ ፡ አምስቱ ፡ ውስጥ) ፡ ከመገኘታቸው ፡ በስተቀር ፤ የጉባኤዎቹ፡ ተካፋዮች ፡ ሽማግሌዎቹና ፡ ባለትዳሮቹ ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ።

58. አንድ ፤ በመንዝ ፡ አጋንጃ ፡ ኪዳነ ፡ ምሕረት ፡ የሚገኙ ፡ ዳኛ ፤ በዚያ ፡ አካባቢ ፡ የሚኖሩ ፡ ወ/ሮ ፡ በለጠች፡ የሚባሉ ፡ ብልህ ፡ ሴት ፡ መኖራቸውንና ፤ ሴትየዋም ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ሁልጊዜ ፡ እንደሚፈለጉ ፡ ገልጸዋል ።

59. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፫፻፲፮/፫ ።

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፤ ለመፋታት ፡ የሚቀርብ ፡ ጥያቄ ፡ ለግልግል ፡ ዳኞቹ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ፡ ይላል ፡ እንጅ ፤ ጥያቄው ፡ በጽሑፍ ፡ መሆን ፡ እንደሚገባው ፡ አይገልጽም ።[60] ሲደረግ ፡ የታየው ፤ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ካልተቆጣጠሯቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፤ በመቶ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ የሚሆኑት ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ በጠበቃ ፡ ወይም ፡ በፍ ርድ ፡ ቤት ፡ ጉዳይ ፡ ጸሐፊ ፡ የተዘጋጀ ፡ የጽሑፍ ፡ ማመልከቻ ፡ ለግልግል ፡ ለዳኞቹ ፡ ቀርቧል ። በአጠናናቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ የተዘወተረው ፡ ከሳሹም ፡ ሆነ ፡ ተከሳሹ ፡ ነገራቸውን ፡ ለግልግል ፡ ዳኞቹ ፡ በቃል ፡ የማስረዳታቸው ፡ ልምድ ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተቆጣጠራቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፤ ከሳሹ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የጽሑፍ ፡ ማመልከቻ ፡ ያቀርብና ፤ ይኸው ፡ ማመልከቻ ፡ በመጀመሪያ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽም ግልና ፡ ዳኝነት ፡ ስብሰባ ፡ ላይ ፡ በሰብሳቢው ፡ ዳኛ ፡ አማካይነት ፡ መነበቡ ፡ የተለመደ ፡ ነው ።

ዳግም ፤ ለዓይነት ፡ በወሰድናቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተቆጣጠራቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የተሾመው ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ የሽምግልና ፡ ጉባኤዎችን ፡ መርቷል ። ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባልተቆጣጠራቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፤ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ (በመቶ ፡ ፹፯ ፡ በሚሆኑት ፡ ውስጥ) ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ በመጀመሪያው ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ ሲመረጥ ፤ ይህ ፡ እድል ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ በእ ድሜ ፡ ለገፋው ፡ ሽማግሌ ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፤ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ሰብሳቢውን ፡ ዳኛ ፡ ሲመርጡ ፤ በጥቂት ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ሾሞ ፡ ተገኝቷል ።

ከባልና ፡ ሚስቱ ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ ምስክሮች ፡ በመቶ ፡ ሃያ ፡ በሚሆኑት ፡ የሽም ግልና ፡ ዳኝነቶች ፡ ውስጥ ፡ ተሰምተዋል ። በቀሩት ፡ ውስጥ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ በስብሰ ባው ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑ ፡ የባለትዳሮቹ ፡ ቤተ ፡ ዘመድና ፡ ጓደኞች ፡ መረጃና ፡ ሃሳብ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ መስጠታቸው ፡ የተለመደ ፡ ቢሆንም ፤ ሽማግሎቹ ፡ ጉዳዩን ፡ የሚሰ ጡት ፡ ከራሳቸው ፡ ከባለጉዳዮቹ ፡ ነው ። ምስክሮች ፡ በተገኙባቸውም ፡ ውስጥ ፡ ምስ ክሮቹን ፡ ያመጣው ፡ እንዲመሰክሩለት ፡ የሚፈልገው ፡ ወገን ፡ ራሱ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፤ ምስክሮች ፡ ከቀረቡባቸው ፡ በመቶ ፡ ሠላሳ ፡ በሚሆኑት ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ሰብ ሳቢው ፡ ዳኛ ፡ ሕጉ ፡ የፈቀደለትን ፡ የጽሑፍ ፡ መጥሪያ ፡ ለምስክሮች ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣኑን ፡ ተጠቅሞበታል ።[61]

ብዙውን ፡ ጊዜ ፤ የሽምግልና ፡ ዳኝነቱ ፡ ኀድ ፡ እሑድ ፡ ቀን ፡ በሰባት ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ የዚያን ፡ ቀን ፡ ስብሰባውን ፡ ጨርሶ ፡ የቤተክርስቲያኑን ፡ ቅጥር ፡ ግቢዎችን ፡ ይለቃል ። ነገር ፡ ግን ፡ በየሳምንቱ ፡ እሁድ ፡ ለዚህ ፡ ዓይነት ፡ ስብሰባ ፡ የሚገናኙ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። በጥናታችን ፤ በጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ውሳኔ ፡ የተፈጸሙት ፡ የሽምግ ልና ፡ ዳኝነቶች ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከተመረጡበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ የመጨረሻው ፡ ውሳኔ ፡ እስከተሰጠበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የፈጁት ፡ ማዕከላዊ ፡ ጊዜ ፡ ፲፱ ፡ ሳምንታት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፤ የተደረጉት ፡ ስብሰባዎችም ፡ ማዕከላዊ ፡ ቁጥር ፡ ከስድስት ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ደርሷል ። በእርቅ ፡ የተፈጸሙት ፡ ደግሞ ፤ ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሶስተ ኛውን ፡ (ማለትም ፡ ፯ ፡ ሳምንታት) ፡ ብቻ ፡ ሲፈጁ ፤ የተደረጉትም ፡ ስብሰባዎች ፡ ማዕ ከላዊ ፡ ቁጥር ፡ አምስት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

በመቶ ፡ ፲፯.፭ ፡ በሚሆኑት ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ የሽማግሌዎች ፡ ለውጥ ፡ ተደር ጓል ። በኢንተርቪው ፡ (ቃል ፡ ጥያቄ) ፡ የተጠየቁት ፡ ሰዎች ፡ ለለውጡ ፡ አዘውትረው ፡

60. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥሮች ፡ ፯፻፳፯ ፤ ፯፻፳፰ ።

61. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፫፻፲፯/፫ ።

የሰጡት ፡ ምክንያት ፡ የተተኪውን ፡ ሽማግሌ ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ መሄድ ፡ ነው ፡፡ ሌሎቹ ፡ ባልተበላለጠ ፡ ደረጃ ፡ የተሰጡት ፡ ምክንያቶች ፤ ሞት ፡ ወይም ፡ ሕመም ፤ በስብሰባዎቹ ፡ አዘውትሮ ፡ አለመገኘት ፡ ወይም ፡ ከሥራው ፡ መሰናበትና ፡ ከሌሎች ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋር ፡ አለመግባባት ፡ ናቸው ፡፡ በአንድ ፡ በመጨረሻ ፡ በተጠቀሰው ፡ የምክንያት ፡ ክፍል ፡ የሚወድቅ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፤ ሁለት ፤ እያንዳንዳቸው ፡ ለያንዳንዱ፡ ነገረተኛ ፡ የሚዘመዱ ፡ ሽማግሌዎች ፤ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ከተለዋወጡ ፡ በኋላ ፡ በቡጢ ፡ ስለተደባደቡ ፤ ሌሎች ፡ ሽማግሌዎች ፡ እስከነጭራሹ ፡ ከሽምግልናው ፡ ጉዳይ ፡ ውጭ፡ እንዲሆኑ ፡ አድርገዋቸዋል ፡፡

ምትክ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነበት ፡ ጊዜ ፤ ተተኪውን ፡ የመምረጡ ፡ ዕድል ፡ በጉባ ዔው ፡ ላይ ፡ ወኪሉን ፡ ላጣው ፡ ባለጉዳይ ፤ ወይም ፡ የባለጉዳዩ ፡ ዘመዶች ፡ ይሰጣል ፡፡[62]

በጊዜው ፡ ልምድ ፡ መሠረት ፤ ሽማግሌዎቹ ፡ በሙሉ ፡ ካልተገኙ ፡ ምንም ፡ ዓይ ነት ፡ ጉባኤ ፡ ስለማይደረግ ፤ የአንድ ፡ ሽማግሌ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ መቅረት፡ በጉዳዩ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ ሁሉ ፡ ከፍተኛ ፡ ችግርን ፡ ሊፈጥር ፡ ይችላል ፡፡

<u>የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ አፈጻጸም ፡፡</u>

የተዘረዘሩ ፡ "ከባድ ፡" መፋታትን ፡ የሚያስከትሉ ፡ ምክንያቶች ፡ ካልተገኙ ፡ በቀር ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ ለማስታረቅ ፡ እንዲሞክሩ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ያዛል ፡፡[63] የሕጉ ፡ አርቃቂ ፡ ከባድ ፡ የመፋታት ፡ ምክንያቶች ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ የማስታረቅ ፡ ጥረት ፡ እንዲደረግ ፡ ያላሳሰቡበት ፡ ምክንያት ፡ ግልጽ ፡ አይደ ለም ፡፡ ለምሳሌ ፤ ከባለትዳሩ ፡ አንደኛው ፡ ከባድ ፡ ከተባሉት ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱን ፡- ዝሙትን ፡- ፈጽሞ ፡ ቢገኝ ፡ እንኳ ፤ ጋብቻው ፡ እንደተጠበቀ ፡ እንዲቆይ ፡ መሞከር ፡ ጠቃሚ ፡ አይሆንምን ? ሌላው ፡ ቢቀር ፤ ኢትዮጵያውያኑ ፡ በዚህ ፡ ያምናሉ ፡፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ገሚስ ፡ በሚሆኑት ፤ ለጥናታችን ፡ ከቀረቡት ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶችን ፡ ያዘሉ ፡ ክሶች ፡ ቢኖሩም ፤ ጋብቻዎቹ ፡ ከፈረሱባቸው ፡ ፳፰ቱ ፡ ነገ ሮች ፡ ውስጥ ፡ የማስታረቅ ፡ ጥረት ፡ ያልተደረገባቸው ፡ ነገሮች ፡ አራት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ለመፋታት ፡ ቢጐተጉትም ፡ እንኳ ፤ የሽም ግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ነገረተኞቹን ፡ የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ ጥያቄ ፡ ባለመቀበል ፡ በግድ ፡ "እንዲታረቁ ፡" አድርገዋቸዋል ፡፡ የዚህም ፡ ውጤት ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ በቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሰላም ፡ አጠራጣሪ ፡ ቢሆን ፤ ባልና ፡ ሚስቱን ፡ በመጨረሻው ፡ አብ ረው ፡ እንዲኖሩ ፡ አድርጓቸዋል ፡፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፤ ለመፋታት ፡ ጥብቅ ፡ ፍላጐት ፡ ያለው ፡ ወገን ፡ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ የሰጡትን ፡ በግድ ፡ "የመታረቅ ፡" ውሳኔ ፡ በዝምታ ፡ አይቀበለውም ፡፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በተዘጋጀበት ፡ ወቅት ፤ አንዲት ፡ በሐረር ፡ የሚገኙ ፡ የቤት ፡ እመቤት ፡ በዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ውሳኔ ፡ ባለመስማማት ፤ የከፍተኛውና ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሽምግ ልና ፡ ዳኞቹ ፡ የሰጡትን ፡ የጋብቻቸውን ፡ መፍረስ ፡ የሚቃረነውን ፡ ብይን ፡ ስላጸና ባቸው ፤ እንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ችሎት ፡ አቤት ፡ እስከማለት ፡ ደርሰዋል ፡፡

በማስገደድ ፡ የሚደረጉ ፡ እርቆች ፡ ሕጋዊነት ፤ በተለይም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የማስታረቅ ፡ ጥረት ፡ ሙከራ ፡ እንኳ ፡ እንዲደረግ ፡ በሚያስገድድባቸው ፤ ከባድ፡

62. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፩፻፸፫/፩ን ፡ ይመለከቷል ፡፡
63. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፩፻፷፯ ፡፡

ምክንያቶች ፡ በተገኙባቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፤ አጠራጣሪ ፡ ነው ።[64] ከባድ ፡ ሁኔታ ዎች ፡ በሌሉባቸውም ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ቢሆንም ፡ የዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አስገድዶ ፡ የማ ስታረቅ ፡ ዘዴ ፡ ተገቢ ፡ አይመስልም ። በእንደዚህ ፡ ዓይነት ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፤ የማስ ታረቁ ፡ ጥረት ፡ ፍሬ ፡ የማይሰጥ ፡ ከሆነ ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ የመ ፋታት ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጡ ፡ ሕጉ ፡ ያስገድዳል ።[65]

ከሁለቱ ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ሳያቀርብ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ለት ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ሕጉ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ መፍቀድ ፡ አለመፍቀዱን ፡ በተ ለይ ፡ የበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እርግጠኛ ፡ ሊሆኑ ፡ አልቻሉም ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ረገድ፡ ሕጉ ፡ በቀላሉ ፡ የሚነበብ ፡ አይደለም ። በቅርቡ ፡ በአንድ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የጠቅላይ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አንዱ ፡ ወይም ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በጋብቻ ፡ አብረን ፡ ለመቆየት ፡ አንፈቅድም ፡ ከማለት ፡ በስተቀር ፡ ተጨማሪ ፡ ምክንያት ፡ ባይሰጡም ፡ እንኳ ፤ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ የማስታረቅ ፡ ጥረት ፡ ተቀባይ ነት ፡ ካላገኘ ፤ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ የመስጠት ፡ ግዴታ ፡ እንዳለባቸው ፡ ገልጿል ።[66]

በጥናታችን ፡ የተካፈሉት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ በጠቅላላው ፤ የማስታረቅ ፡ ጥረት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ለመታረቅ ፡ እንቢተኛ ፡ ሆኖ፡ በተገኘ ፡ ቁጥር ፡ የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ ፈቅደዋል ። እንዲሁም ፡ ሁለቱም ፡ ወገ ኖች ፡ ለመፋታት ፡ መፈለጋቸውን ፡ ደጋግመው ፡ በገለጹበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የጋብቻ ቸው ፡ መፍረስ ፡ ተፈቅዶላቸዋል ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ሊታወስ ፡ የሚገባው ፤ ሕጉ ፡ "በባ ልና ፡ ሚስት ፡ ስምምነት ፡ የሚደረግ ፡ መፋታትን ፡"[67] መሆኑን ፡ ነው ። ይህም ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ በግል ፡ ስምምነታቸው ፡ "ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡" ማፋታት ፡ አይ ችሉም ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህን ፡ ከማድረጋቸው ፡ በፊት ፤ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ በቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ አማካይነት ፡ ለሚደረግ ፡ የእርቅ ፡ ሙከራ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ።[68]

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፤ የእርቁ ፡ ሙከራ ፡ ያልተሳካ ፡ እንደሆነ ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ ሊፈቀድ ፡ የሚያስፈልግበትን ፡ አንዳንድ ፡ የጊዜ ፡ ወሰን ፡ ደንግጓል ። በአ ማርኛ ፡ ቋንቋ ፤ በተፃፈው ፡ መደበኛ ፡ (ኦፊሲየል) ሕግ ፡ መሠረት ፤ የጋብቻውን ፡ መጽ ናት ፡ ሊያፈርስ ፡ የሚችል ፡ ከፍተኛ ፡ ምክንያት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፤ የመፋታት ፡ ጥያቄ ፡ ከቀረበበት ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ መሰጠት ፡ አለበት ።[69] በጥናታችን ፡ ተካፋይ ፡ የሆኑት ፡ ሽማግሌዎች ፤ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ሥራቸው ፡ በዘፈቀደ ፡

---

64. ከዚያው ።

65. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፮፻፸፰ ።

66. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፭፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ የሸዋ ፡ ልዑል ፡ ኃይለ ፡ ማርያምና ፡ የደበበ ፡ ኃይሌ ፡ ጉዳይ ፡ በተጨማሪም ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፭፯ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የትርፌ ፡ መአሾንና ፡ የአብር ሽት ፡ ገብረ ፡ መስቀልን ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከቷል ።

67. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፮፻፷፮/፩

68. የምንትዋብ ፡ ተዘራና ፡ የኋላ ፡ እሸት ፡ ዳምጤ ፡ ጉዳይ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፷፩ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፹፩/፶፯) ፡ (ያልታተመ) ፡ በተጨማሪም ፤ የለወጠኝ ፡ መታፈሪ ያንና ፡ የእጅግአየሁ ፡ ደንቦባን ፡ ጉዳይ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፷ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፬፻፴፯/፷) ፡ (ያልታተመ) ይመለከቷል ። በዚህም ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፤ ባለጉዳዮቹ፡ ለመፋታት ፡ ያደረጉትን ፡ ስምምነት ፡ በሦስት ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ ፈርመው ፡ ሲያበቁ ፤ የአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አጽድቆላቸው ፡ ነበር ። የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ስላልተመለከቱት ፡ ብቻ ፡ የበታቹን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ሽሮ ፡ መልሶታል ።

69. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፮፻፷፰ ።

ሲከናወን ፡ የቆየ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፤ የሕጉ ፡ "የመጀመሪያው ፡" ቅጅ ፤[70] የእንግሊዝኛውንና ፡ የፈረንሳዊኛውን ፡ ቅጅዎች ፡ ጨምሮ ፡ በ"ሦስት ፡ ወር ፡" ውስጥ ፡ ስለሚሉ ፡ ሳይሆን ፡ አልቀረም ። የሽምግልና ፡ ጉባኤዎችን ፡ በሳምንት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ መደረግ ፡ ጠቅላላ ፡ ልምድ ፡ ከተመለከትን ፤ ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ በሚገኙባቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠት ፡ በፊት ፡ የማስታረቅ ፡ ሙከራ ፡ መደረግ ፡ እንደሚገባው ፡ ሁሉ ፡ የሚደረግ ፡ ከሆነ ፤ የአንዱ ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ በእርግጥም ፡ አጭር ፡ ይሆናል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ ዝሙትን ፡ ወይም ፡ ጠፍቶ ፡ መሄድን የመሰለ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ባለትዳሩ ፡ የጋብቻቸውን ፡ መፍረስ ፡ ያለማቋረጥ ፡ የሚሻ ፡ ከሆነ ፤ ተበዳዩን ፡ ወገን ፡ ሌላ ፡ ሕጋዊ ፡ ግንኙነት ፡ እንዳይመሰርት ፡ አድርጎ ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ በጋብቻው ፡ ታስሮ ፡ እንዲቆይ ፡ ማድረግ ፡ ተገቢ ፡ አይሆንም ። የአማርኛው ፡ ቋንቋ ፡ መደበኛው ፡ የሕጉ ፡ ቅጅ ፡ "ሦስት ፡ ወር ፡" ተብሎ ፡ እንዲነበብ ፡ መሻሻል ፡ ይገባዋል ።

መፋታትን ፡ ሊያስከትል ፡ የሚችል ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ የሌለ ፡ እንደሆነና ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ የጊዜውን ፡ መራዘም ፡ በስምምነት ፡ ካልፈቀዱ ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ የማስታረቅ ፡ ሙከራቸው ፡ ካልተሳካ ፡ የመፋታቱ ፡ ጥያቄ ፡ በቀረበላቸው ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ "ውስጥ ፡" የፍቺውን ፡ ብይን ፡ መስጠት ፡ እንዳለባቸው ፡ ሕጉ ፡ ያዛል ።[71] ይህንም ፡ ማለት ፤ ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ እንደተገኙባቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ እንደሚደረገው ፡ ሁሉ ፤ የፍቺው ፡ ብይን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መሰጠት ፡ አለበት ፡— ይኸውም ፤ የማስታረቁ ፡ ሙከራ ፡ የማይሳካ ፡ ከሆነ ፡ ባለትዳሮቹን ፡ በጋብቻቸው ፡ ተሳስረው ፡ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ እንዲቆዩ ፡ እንዳይገደዱ ፡ ለማድረግ ፡ ጊዜው ፡ ሳይተላለፍ ፡ መስጠት ፡ አለበት ።[72] የአንዱ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ከማለፉ ፡ በፊት ፡ የፍቺው ፡ ብይን ፡ ሊሰጥ ፡ አይቻልም ፡ በማለት ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቅርቡ ፡ የሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ከላይ ፡ በተገለጸው ፡ ትርጓሜ ፡ ላይ ፡ ጥርጣሬን ፡ ሳያሳድር ፡ አይቀርም ።[73] ቢሆንም ፤ ይህ ፡ አስተያየት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እግረ ፡ መንገዱን ፡ የተናገረው ፡ እንጅ ፤ ቀርቦለት ፡ ለነበረው ፡ ጉዳይ ፡ ውሳኔ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ አልነበረም ። ይህንን ፡ ጭብጥ ፡ በቅርብ ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ በቀረበለት ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጉዳዩን ፡ ሳያብራራው ፡ አይቀርም ።

የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ በሥራቸው ፡ ላይ ፡ ቸልተኛ ፡ ከሆኑና ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ የፍቺውን ፡ ብይን ፡ ካልሰጡ ፤ አንደኛው ፡ ወገን ፡ በሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፤ ተገቢው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሽማግሌዎቹ ፡ ነገሩን ፡ ወስዶ ፡ ሊመረምረው ፡ እንደሚችል ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ይናገራል ።[74]

---

70. ደብልዩ ፡ ቡሐጅያር ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፫ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፺ ።
71. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፲፻፸፰ ።
72. አር ፡ ዴቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፰ ። አንድ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙ ፡ ጠበቃ ፤ ወደእሳቸው ፡ የሚሄዱት ፡ ነገረተኞች ፡ ስለአዲሶቹ ፡ ሕጎች ፡ ምን ፡ ያስባሉ ፤ ለሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ሲመልሱ ፤ "የአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የተሻለ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፤ ቤተዘመድ ፡ ነክ ፡ ጉዳዮች ፡ በልማድ ፡ ይሠራ ፡ በነበረው ፡ ዓይነት ፡ ቢፈጸሙ ፡ ይፈቅዳሉ ። ለምሳሌ ፤ የቤተ ፡ ዘመድ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ውሳኔ ፡ እስኪሰጡ ፡ ድረስ ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጡ ፡ ማድረጉ ፡ ትክክለኛ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤" ብለዋል ።
73. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ የሸዋ ፡ ልዑል ፡ ኃይለማርያምና ፡ የደበበ ፡ ኃይሌ ፡ ጉዳይ ።
74. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፲፻፴፪ ። ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ በተጠቀሰው ፡ በሸዋ ፡ ልዑል ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ጉዳይ ፤ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ከሰባት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ በጉዳዩ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ እርምጃ ፡ ሳያደርጉ ፡ በመቅረታቸውና ፤ ለዚህም ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ባለማቅረባቸው ፤ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጉዳዩን ፡ ወስዶ ፡ እራሱ ፡ ወስኖታል ።

የፍቺ ፡ ውሳኔ ፡ አሰጣጥ ፤

ለምሳሌ ፡ ባጠናናቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፤ የፍቺው ፡ ውሳኔ ፡ ይሰጥ ፡ አይሰጥ ፡ በማለት ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ በሽምግልናው ፡ ዳኝነት ፡ ፍጻሜ ፡ ላይ ፡ ድምጽ ፡ የሰጡባቸውና ፡ የአብዛኛውም ፡ ድምጽ ፡ ተሰሚነት ፡ ያገኘባቸው ፡ ጥቂት ፡ ነገሮች ፡ ተገኝተዋል ።[75] ሆኖም ፡ ከላይ ፡ ለተዘረዘሩት ፡ ምክንያቶች ፡ ይህ ፡ አሰራር ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ።

ተጋቢዎቹ ፡ ሳይስማሙ ፡ የቀሩ ፡ እንደሆነ ፡ የመፋታት ፡ ብይን ፡ እንዲሰጥ ፡ ሕጉ ፡ ይጠይቃል ፤ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ምርጫ ፡ ስለሌላቸው ፡ ድምጽ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። መደረግ ፡ የሚገባው ፤ የፍቺው ፡ ምክንያት ፡ (የሚፈጸመውን ፡ የንብረት ፡ ቅጣት ፡ ለመወሰን ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ፦ ወደፊት ፡ የሚሰጠውን ፡ ገለጻ ፡ ተመልከት)፡[76] ከባድ ፡ መሆኑን ፡ ወይም ፡ አለመሆኑን ፡ የሚያሳይ ፡ መግለጫና ፤ የማስታረቅ ፡ ጥረት ፡ ተደርጐ ፡ ሳይሳካ ፡ መቅረቱን ፤ ስለዚህም ፡ የጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ መታዘዙን ፡ የሚያመለክተውን ፡ የፍቺ ፡ "ውሳኔ ፡" መጻፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፤ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ በተገኘበት ፡ ጊዜ ፤ በዚሁ ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ የመፋታቱ ፡ ውሳኔ ፡ ከተሰጠ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ባልበለጠ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡[77] በሚሰጥ ፡ ተጨማሪ ፡ ውሳኔ ፤ የነገረተኞቹን ፡ ንብረትና ፡ ልጆች ፡ ስለሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ የወሰኑትን ፡ መግለጽ ፡ ይገባል ። ስለእነዚህ ፡ በመጨረሻ ፡ ስለተጠቀሱት ፡ ጭብጦች ፡ በግልግል ፡ ዳኞቹ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የተፈጠረ ፡ እንደሆነ ፡ በድምጽ ፡ ብልጫ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።[78]

በመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ የሚፈጸሙ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነቶች ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ የጽሑፍ ፡ ውሳኔ ፡ የማዘጋጀቱ ፡ ጉዳይ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ የታዘዘ ፡ ሲሆን ፤[79] ለጥናታችን ፡ ከቀረቡት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተቆጣጠራቸው ፡ ነገሮችም ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ ይኸው ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቧል ።[80]

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባልተቆጣጠራቸው ፤ ለምሳሌ ፡ በወሰድናቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ በመቶ ፡ ሃያ ፡ አራቱ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የጽሑፍ ፡ ውሳኔ ፡

75. በተጨማሪም ፤ የመፋታት ፡ ብይን ፡ የመስጠቱን ፡ ጉዳይ ፡ ተገቢነት ፡ ለመወሰን ፡ ድምፅ ፡ ሊሰጥ ፡ ሲል ጉዳዩን ፡ ጥለው ፡ የሄዱ ፡ ሁለት ፡ የግልግል ፡ ዳኞች ፡ የተገኙበትን ፡ የጌጤነሽ ፡ በቀለንና ፡ የሙሉነህ፡ አዘነን ፡ ጉዳይ ፤ (ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፷፩ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር፡ ፱፻፴፩/፷፩) (ያልታተመ) ፡ ይመለከቷል ። የቀሩት ፡ ሦስት ፡ ሽማግሌዎች ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ወሰኑ ። የከፍተኛውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ በብዙ ፡ ምክንያቶች ፡ ውሳኔውን ፡ ሽሮ ፤ ሌላ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ በአዲስ ፡ የግልግል ፡ ዳኞች ፡ አማካይነት ፡ እንዲደረግ ፡ አዞ ፤ ጉዳዩን ፡ ለአውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ መልሶታል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ በማድረግ ፤ የመፋታቱን ፡ ውሳኔ ፡ ሁሉም ፡ የቤተዘመድ ፡ የግልግል ፡ ዳኞች ፡ መፈረም ፡ እንደሚገባቸው ፡ ማሳየቱ ፡ እንደሆነ ፤ የፈጸመው ፡ ትክክለኛ ፡ ውሳኔ ፡ ነው ። (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፫፻፲፰/፬ ፦ እርቅ ፡ የማይቻል ፡ ከሆነ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ድምጽ ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ ባይሆንም ፤ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ እንዳለባቸው ፤ ሕጉ ፡ ያዛል ።

76. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የሸዋልዑል ፡ ኃይለማርያምን ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከቷል ።

77. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥሮች ፡ ፯፻፸፱—፯፻፹ ።

78. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፫፻፲፰/፫ ።

79. ቀጥተኛ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፫፻፲፰/፬ን ፡ ይመለከቷል ።

80. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፤ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቁጥጥር ፡ ሥር ፡ የተደረገ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ ጉዳይ ፡ በእርቅ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፤ ሁለቱ ፡ ባለጉዳዮች ፡ የፈረሙበት ፡ "ስምምነት ፡" ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲቀርብ፡ ይደረጋል ። ይኸን ፡ ማድረጉ ፡ ግን ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ።

አልተዘጋጀላቸውም ።[81] ከቀሩትም ፡ ውስጥ ፣ ጽሑፉ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የቀረበባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ በመቶ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። በተረፉት ፡ ውስጥ ፡ የውሳኔዎች ፡ ቅጅዎች ፡ ለባለጉዳዮቹ ፡ ይሰጣሉ ፡ ወይም ፡ በሰብሳቢ ፡ ዳኛው ፡ እጅ ፡ ይቀመጣሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ለቄስ ፡ ተሰጥቷል ። ይህም ፡ የሚያሳየው ፣ በመቶ ፡ ዘጠና ፡ አንድ ፣ በሚሆኑት ፣ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተቆጣጠራቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ ሳይበልጡ ፡ የማይቀሩት ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ቁጥጥር ፡ ውጭ ፡ የተፈጸሙ ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔዎች ፡ ዘለቄታነት ፡ ባለው ፡ አኳኋን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የመመዝገብ ፡ እድል ፡ እንደማይገጥማቸው ፡ ነው ። ይህም ፡ ወደፊት ፡ ለባለጉዳዮቹ ፡ መጥፎ ፡ ውጤትን ፡ ሊያስከትል ፡ ይችላል ፣ ለምሳሌም ፣ አንደኛው ፡ ወገን ፡ ያገባ ፡ እንደሆነና ፡ ጋብቻው ፡ ሕጋዊ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመ ፡ ጋብቻ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ በተከተለ ፡ ጊዜ ፡ የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ ሊመሰክሩ ፡ ከሚችሉት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ውስጥ ፡ አንዱም ፡ የማይገኝ ፡ እንደሆነ ፡ የሚፈጠረውን ፡ ችግር ፡ ማሰብ ፡ ይበቃል ።[82]

ከዚህም ፡ የተነሳ ፣ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ ሕጉ ፡ ውስጥ ፣ አናቅጽ ፡ በመጨመርም ፡ ቢሆን ፣ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የፈጠሩትን ፡ የጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ ችግሮች ፡ የሚመለከተውን ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነትን ፡ የመቆጣጠር ፡ ልምድ ፡ ማበረታታት ፡ ያስፈልጋል ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡[83] ስለ ፡ ክብር ፡ መዝገብ ፡ ያሰፈረው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋልገና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የቀረው ፡ የሚመስለው ፡ ሕግ ፣ የጋብቻዎች ፡ መፍረስ ፡ ይመዝገብ ፡ ብሎ ፡ በግልጽ ፡ አይናገርም ። ቢናገርም ፡ እንኳ ፡ ደግሞ ፣ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የማይቆጣጠራቸው ፡ ነገሮች ፡ ሰብሳቢ ፡ ዳኛ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ መሃይም ፡ ስለሆነ ፡ ውሳኔው ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ በተገቢው ፡ ቦታ ፡ መመዝገቡ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሚጠበቅ ፡ አይሆንም ።[84] ከዚህ ፡ ጋር ፡ አያይዘን ፡ ልንመለከተው ፡ የሚገባ ፣ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካልተቆጣጠራቸው ፡ ነገሮች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ውስጥ ፡ ጠበቃ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የሕግ ፡ እውቀት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ጓድ ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በቀሩት ፡ ዘጠና ፡ ሁለት ፡ በመቶ ፡ በሚሆኑት ፡ ውስጥ ፡ ግን ፣ ሽማግሌዎቹ ፡ ከማንም ፡ ሰው ፡ የሕግ ፡ አስተያየት ፡ አልጠየቁም ።

## ሕፃናትና ፡ ንብረት ፣

## የጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ እንዲያሰናክሉ ፡ የታቀዱ ፡ ዘዴዎች ፣

ለምሳሌ ፡ ባጠናናቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፣ በጠቅላላው ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ያልሞላቸው ፡ ወንድም ፡ ሆኑ ፡ ሴት ፡ ሕፃናት ፡ ከእናትየዋ ፡ ጥበቃ ፡ ሥር ፡ እንዲውሉ ፡

---

81. በተለይ ፡ በአሥመራ ፡ የሚደረጉ ፡ የግልግል ፡ ዳኝነቶች ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ አሠራር ፡ አይታይባቸውም።
82. በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻ ፡ መፈጸም ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፭፻፹፭ ፡ የተከለከለ ፡ ሲሆን ፣ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፣ ቁጥሮች ፡ ፯፻፲፬/፫ ፣ ፯፻፲፭ ፣ ፯፻፲፮ መሠረትም ፡ የሚያስቀጣ ፡ ነው ።
ጂ ፡ ቫንደርሲንደን ፣ "ማኑዋል ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ፋምሊ ፡" (፲፱፻፷፱) ፡ (ያልታተመ) የረቂቁ ፡ ገጽ ፡ ፳፬ ፡ ላይ ፣ በጋብቻ ፡ ላይ ፡ ጋብቻን ፡ በመፈጸም ፡ ረገድ ፡ ስላለው ፡ ጉዳይ ፡ ሲናገሩ ፣ "(ሌላ ፡ ጋብቻን ፡ ለመፈጸም) ፡ አንደኛው ፡ የትዳር ፡ ጓደኛ ፡ ሞቷል ፡ ብሎ ፡ ማረጋገጥ ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ሁሉ ፡ ጋብቻው ፡ መፍረሱን ፡ ማስረዳት ፡ የዚያኑ ፡ ያህል ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።"
83. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፣ ቁጥር ፡ ፶፱ና ፡ ተከታዮቹ ።
84. ምንም ፡ እንኳ ፣ በ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ብቻ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ የተመዘገቡት ፡ የብሔራዊ ፡ ጋብቻዎች ፡ ቁጥር ፡ ፪ሺ፫፻፷፯ ፡ ሲደርስ ፣ በአለፉት ፡ ሰባት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ በብሔራዊ ፡ ጋብቻዎች ፡ መዝገብ ፡ የሠፈሩ ፡ የመፋታት ፡ ብይኖች ፡ "አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡" ቢሆን ፡ ነው ። በከተማው ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸሙት ፡ ብሔራዊ ፡ ጋብቻዎች ፡ በመቶ ፡ አሥር ፡ ብቻ ፡ ሲሆኑ ፣ የቀሩት ፡ የሃይማኖትና ፡ የልማድ ፡ ጋብቻዎች ፡ ናቸው ። ከአቶ ፡ ልዑል ፡ ሰገድ ፡ በቀለ ፣ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የሕዝብ ፡ ቆጠራና ፡ የማሕበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ጉዳይ ፡ ክፍል ፡ ተባባሪ ፡ ዲሬክተር ፡ ጋር ፡ የካቲት ፡ ፩ ፣ ፲፱፻፷፭ ፣ የተደረገ ፡ ውይይትና ፣ "ዘ ፡ ኢትዮፒያን ፡ ሄራልድ ፣" ኅዳር ፡ ፴፤ ፲፱፻፷፰፤ ገጽ ፡ ፩ ፣ ፪ኛ ፡ ዓምድ ፡ ይመለከቷል ።

ሲደረግ ፤ ከዚያ ፡ በላይ ፡ የሆኑትን ፡ ደግሞ ፡ አባትየው ፡ እንዲቆጣጠራቸው ፡ ተደርጓል ።[85] ምንም ፡ እንኳ ፡ በባልና ፡ ሚስት ፡ መለያየት ፡ የተነሳ ፡ የፈረሱ ፡ ቤተሰቦችን ፡ ጉዳይ ፡ እየተከታተልን ፡ ጥናት ፡ ባናደርግም ፤ አሁን ፡ የሚሠራበት ፡ ልምድ ፡ ወንድም ፡ ሆኑ ፡ ሴት ፡ ሕፃናት ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሲሞላቸው ፤ ፈቃደኛ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ ለአባትየው ፡ መስጠት ፡ ነው ።[86] የዚህም ፡ ልምድ ፡ መሠረት ፤ አንድ ፡ ልጅ ፡ በሕፃንነቱ ፡ ወራት ፡ የእናቱ ፡ ጥበቃ ፡ አስፈላጊው ፡ ሲሆን ፤ ከአደገ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለአባቱ ፡ ጠቃሚ ፡ ረዳት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ ነው ።

ብዙውን ፡ ጊዜ ፤ የግልግል ፡ ዳኞቹ ፡ ሕፃናቱ ፡ በእናታቸው ፡ ጥበቃ ፡ ሥር ፡ እስካሉ ፡ ድረስ ፤ ለዚሁ ፡ ተግባር ፡ ይውል ፡ ዘንድ ፡ አባትየውን ፡ የተወሰነ ፡ የማሳደጊያ ፡ ገንዘብ ፡ ለእናትየዋ ፡ እንዲሰጥ ፡ ይወስናሉ ። ለምሳሌ ፡ ካጠናናቸው ፡ ነገሮች ፡ በሁለቱ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ክፍያ ፡ ሕፃኑ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሲሆነው ፡ እንደሚቋረጥ ፡ ሲጠቅስ ፤ በቀሩትም ፡ ውስጥ ፡ ምናልባት ፡ የዚሁ ፡ ዓይነት ፡ መግባባት ፡ ሳይኖር ፡ አልቀረም ።

በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምክንያቶች ፡ የሕፃናትን ፡ ይዞታ ፡ የሚመለከተው ፡ የተለመደ ፡ መንገድ ፡ የተለያየ ፡ ነው ። በአንድ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፤ እናትየዋ ፡ ልጅዋን ፡ ስላጉላላችው ፡ ሕፃኑ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሳይሆነው ፡ ለአባትየው ፡ እንዲሰጥ ፡ ተደርጓል ። በአንድ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ አባትየው ፡ ዓይነ ፡ ስውርና ፡ ሥራፈት ፡ በመሆኑ ፡ ማሳደጊያ ፡ እንዲከፍል ፡ ሳይጠየቅ ፡ ቀርቷል ።

ለምሳሌ ፡ ባጠናናቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ በአንዳቸውም ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፤ የጋራ ፡ ንብረታቸውን ፡ ክፍያ ፡ ወይም ፡ ሚስትየዋ ፡ ለትዳርዋ ፡ ይረዳት ፡ ዘንድ ፡ ይዛው ፡ የመጣችውን ፡ ንብረትዋን ፡ የሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፤ የቀድሞው ፡ ባል ፡ ለቀድሞ ፡ ሚስቱ ፡ በየጊዜው ፡ የገንዘብ ፡ እርዳታ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተጠይቆ ፡ አያውቅም። እንዲህ ፡ ዓይነቱ ፤ በአንዳንድ ፡ ሀገሮች ፡ ለሕይወት ፡ ድጋፍ ፡ የሚሰጥ ፡ ገንዘብ ፡ (alimony) ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ክፍያ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ባህል ፡ ውስጥ ፡ ያልታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ።[87] ቢሆንም ፤ ሚስትየዋ ፡ ጉዳይዋ ፡ በመሰማት ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ የእርዳታ ፡ ገንዘብ ፡ ሲሰጣት ፤ ጉዳዩ ፡ በጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደሆነ ፡ ይኸው ፡ ገንዘብ ፡ ከሴትየዋ ፡ ድርሻ ፡ ላይ ፡ ተቀናሽ ፡ ይሆናል ።

በቃል ፡ ጥያቄዎቹ ፡ መልስ ፡ እንደተገለጸው ፤ ባለትዳሮቹ ፡ ጋብቻቸው ፡ በፈረሰ ፡ ጊዜ ፤ የማይንቀሳቀሰውንም ፡ ሆነ ፡ የግል ፡ ንብረታቸውን ፡ እኩል ፡ በእኩል ፡ መካፈላቸው ፡ የተለመደ ፡ ነው ። አንደኛው ፡ ወገን ፡ አምጥቶት ፡ እባለትዳሩ ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ የተደባለቀውን ፡ ንብረት ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ መለየት ፡ ከቻሉ ፤ (ይህም ፡ ቀላል ፡ ሥራ ፡ አይደለም) ፡ ይህን ፡ ሀብት ፡ ለግል ፡ ባለንብረቱ ፡ መልሰው ፡ ሲያበቁ ፤ በጋብቻው ፡ ዘመን ፡ የተገኘውን ፡ የጋራ ፡ ንብረት ፡ ደግሞ ፡ እኩል ፡ በእኩል ፡ ያካፍሏቸዋል ።[88] በአንድ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ የስድስት ፡ ክፍል ፡ መደዳ ፡

85. በተጨማሪ ፤ የተሾመ ፡ ገዛኸኝንና ፡ የተዋበች ፡ መኰንን ፡ ጉዳይ ፤ (የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፤ ፲፱፻፷ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፶፱/፷) ፡ (ያልታተመ) ፡ (የአሥራ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ለአባትየው ፡ የተሰጠችበትን) ፡ ይመለከቷል ። አልፎ ፡ አልፎም ፤ ከሰባት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ለሆነ ፡ ልጅ ፡ ከማን ፡ ጋር ፡ ለመኖር ፡ እንደሚፈልግ ፡ የመምረጥ ፡ እድል ፡ ይሰጠዋል ።

86. ሃርትል ፡ ሜየር ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፰ ፡ የተጠቀሰ ፤ ገጽ ፡ ፴፰ ። በተጨማሪም ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የትርፌ ፡ ምአሾንና ፡ የአብርኸት ፡ ገብረ ፡ መስቀልን ፡ ጉዳይ ፡ ይመለከቷል ።

87. ኤን ፡ ማርየን ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፮ ፡ የተጠቀሰ ፤ ገጽ ፡ ፩፻፳፫ ።

88. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥሮች ፡ ፯፻፺-፯፻፺፩ ፤ ፯፻፹፫—፯፻፹፱ ፡ ይመለከቷል ።

ቤቶች ፡ ባለቤቶች ፡ ነበሩ ። ሲካፈሉም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ሦስት ፡ ክፍል ፡ እንዲወስዱ፡ ተደርጓል ። ይኸ ፡ እኩል ፡ በእኩል ፡ የማካፈል ፡ ሥርዓት ፡ እንዲለወጥ ፡ ያደረጉ ፡ ብዙ ፡ የተለያዩ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ። ለምሳሌም ፤ በአንድ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ባልየው ፡ የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ አጥብቆ ፡ ከመፈለጉ ፡ የተነሳ ፤ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ይረዳው ፡ ዘንድ ፡ ባለቤቱ ፡ የጋራ ፡ ንብረታቸውን ፡ በሙሉ ፡ እንድትወስድ ፡ ተስማምቷል ።

ቀደም ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሱት ፤ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ደራሲ ፡ የፈጠሯቸው ፡ "የጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ እንዲያሰናክሉ ፡ የታቀዱ ፡ ዘዴዎች ፡"[89] ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ዓይነት ፡ እንዲሠሩ ፡ የታሰቡ ፡ ነበሩ ። ከባድ ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ ተገኝቶ ፡ መፋታትን ፡ ካስከተለ ፡ "እንደ ፡ ደንቡ ፡" ከሆነ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በአፈፃጸሙ ፡ ላይ ፡ የግል ፡ ምርጫ ፡ ቢኖራቸው ፤ ከባዱን ፡ ጥፋት ፡ ፈጽመሀል ፡ ከተባለው ፡ ወገን ፡ ከፍተኛው ፡ ልክ ፡ የተወሰነ ፡ ንብረት ፡ ወስደው ፡ ለሌላው ፡ ወገን፡ መስጠት ፡ ይኖርባቸዋል ። ይህም ፡ ባልና ፡ ሚስቱን ፡ ከባድ ፡ በሆነ ፡ አኳኋን ፡ የጋብቻ፡ ግንኙነታቸውን ፡ የሚያበላሽ ፡ ነገሮችን ፡ እንዳይፈጽሙና ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ እንዳይፋቱ ፡ ለማገድ ፡ የታቀደ ፡ ነው ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖር ፡ ጋብቻው ፡ የፈረሰ ፡ እንደ ሆነ ፤ ሽማግሌዎቹ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ የግል ፡ ምርጫ ፡ ቢኖራቸው ፤ "እንደ ፡ ደንቡ ፡" ከሆነ ፤ "የመፋታቱን ፡ ጥያቄ ፡" ያቀረበውን ፡ ወገን ፡ እኩል ፡ ባልሆነ ፡ የንብረት ፡ ክፍያ ፡ መቅጣት ፡ ይኖርባቸዋል ። ይኸም ፡ ባለትዳሮቹ ፡ በአንዳንድ ፡ ምክንያት ፡ ትዳራቸውን ፡ በመሰልቸት ፡ የጋብቻቸውን ፡ መፍረስ ፡ ከመሻት ፡ እንዲቆጠቡ ፡ ለማድረግ ፡ የታቀደ ፡ ነው ።

ለዓይነት ፡ በተመለከትናቸው፡ ነገሮች ፤ በመፋታቱ ፡ ጥያቄ ፡ ውስጥ ፡ የከባድ ፡ ምክንያት ፡ መኖር ፡ ከተመለከተባቸውና ፡ ተከሳሹም ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘባቸው ነገሮች ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ሦስተኛ ፡ በሚሆኑት ፡ ውስጥ ፤ ጥፋተኛው ፡ ንብረቱን ፡ እኩል ፡ እንዳይካፈል ፡ ተበይኖበታል ። ዳሩ ፡ ግን ፤ በአንዳቸውም ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖር ፡ የመፋታት ፡ ጥያቄ ፡ ስላቀረበ ፡ ብቻ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የተቀጣ ፡ ወገን ፡ አልነበረም ። ከዚህም ፡ በላይ ፤ የንብረት ፡ ቅጣት ፡ ባለመስጠቱ ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሽማግሌዎቹን ፡ ውሳኔ ፡ የለወጠበት ፡ (ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጠቀሰ) ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ተገኝቷል ።

ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ባልተገኘባቸው ፡ ነገሮች ፡ ውስጥ ፤ አመልካቾቹ ፡ ያልተቀጡበትን ፡ ምክንያት ፡ ማግኘት ፡ አያዳግትም ። በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሁሉ ፤ ጥፋቱ ፡ የማንም ፡ ይሁን ፤ ወይም ፡ የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ የፈለገው ፡ ታወቀም ፡ አልታወቀም ፤ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የመፋታት ፡ ጥያቄ ፡ የሚያቀርቡት ፡ ሴቶች ፡ ናቸው ። ባልየው ፡ ንብረቱን ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ ሚስቱን ፡ ማባረሩና ፤ ከዚህም ፡ የተነሳ ፡ ሚስትየዋ ፡ ድርሻዋን ፡ ለማግኘት ፡ ስትል ፡ ክስ ፡ እንድትጀምር ፡ ማድረጉ ፡ የተለመደ ፡ ነው ።[90] በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አመልካቾቹ ፡ ይቀጡ ፡ የሚለውን ፡ የሕጉን "ጠቅላላ ፡ ደንብ ፡" በሥራ ፡ ላይ ፡ አለማዋል ፡ ትክክለኛ ፡ ውሳኔ ፡ ነው ።

ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ባልተገኘበት ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ አመልካቹ ፡ እኩል ፡ ባልሆነ ፡ የንብረት ፡ ክፍያ ፡ እንዲቀጣ ፡ የተደረገበት ፡ አንዱ ፡ ምሳሌ ፤ በቅርቡ ፡ የጠቅላይ ፡

89. ከላይም ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፰፱ን ፡ ይመለከቷል ።

90. እርግጥ ፤ አንድ ፡ ከሳሽ ፡ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ "ችግራችንን ፡ ያስወግዱልን ፡" ብሎ ፡ ሊጠይቅና ፡ በዚህም ፡ ዓይነት ፡ "የመፋታት ፡ ጥያቄ ፡" ከማቅረብ ፡ ሊቆጠብ ፡ ይችላል ፡ ዳሩ ፡ ግን ፤ ይህ ፡ ዜና ፡ በኅብረሰቡ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙት ፡ ሴቶች ፡ ይደርሳል ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ።

ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ነው ።[91] ዳሩ ፡ ግን ፤ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ የተበየነው ፡ ቅጣት ፡ አመልካችዋ ፡ ጥያቄዋን ፡ በማቅረብዋ ፡ ምክንያት ፡ ብቻ ፡ የተሰጠ ፡ አልነበረም ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አተኩሮ ፡ የተመለከተው ፤ የማስታረቁ ፡ ሙከራ ፡ በሚደረግበት ፡ ወቅት ፡ አመልካችዋ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ያለማቋረጥ ፡ መወትወቷን ፡ ነው ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፤ "ለቤትና ፡ ለልጆችዋ ፡ ስትል ፡ የመፋታቱን ፡ ጥያቄ ፡ እርግፍ ፡ አድርጋ ፡ መተው ፡ ይገባት ፡ ነበር ፡" ብሏል ። ከባድ ምክንያት ፡ ባልተገኘበት ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ቅጣት ፡ መስጠት ፡ ያለበት ፡ ከሆነ ፤ ይህ ፡ እርቅን ፡ እንቢ ፡ በማለት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተው ፡ ምክንያት ፡ እሕጉ ፡ ውስጥ ፡ አሁን ፡ ካለው ፡ "ጥያቄውን ፡ ያቀረበውን ፡" ሰው ፡ ከሚመለከተው ፡ ምክንያት ፡ ይበልጥ ፡ ትክክለኛ፡ ይመስላል ።[92]

ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ይሰራበት ፡ የነበረውን ፡ ኤውሮፓዊ ፡ ሚዛን ፤ ማለትም ፡ የማይስማሙ ፡ የማይጣጣሙ ፡ ባለትዳርን ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ በተፈቀደ ፡ ቁጥር ፡ አንደኛውን ፡ ወገን ፡ በመቅጣት ፡ እንዳይለያዩ ፡ የሚደረገውን ፡ ሙከራ ፤ በኢትዮጵያዊው ፡ ኅብረ ፡ ሰብ ፡ ላይ ፡ መጫን ፡ ተገቢ ፡ መሆኑ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ። በምዕራባውያን ፡ ሀገሮች ፡ አሁን ፡ የተጀመረው ፡ ውሳኔው ፡ አስቸኳይ ፡ እንዳይሆን ፡ ባለትዳሮቹን ፡ ለተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ አብረው ፡ እንዲቆዩ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፤ አለመስማማት፡ ከተፈጠረ ፤ ስምምነት ፡ ማጣቱ ፡ ብቻውን ፡ ለጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን፡ ይችላል ፡ የሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ አስገራሚ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።[93] የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ አርቃቂም ፡ እራሳቸው ፤ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ በሚመለከተው ፡ የሕጉ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ በሰጡት ፡ አንድ ፡ ማብራሪያ ፡ ውስጥ ፤ ይህንን ፡ ዝንባሌ ፡ የተገነዘቡት፡ ይመስላል ።[94] ከሕጉ ፡ በፊት ፡ እንደነበረው ፡ ልማድ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባለትዳሮቹን ፡ ለማስታረቅ ፡ በቤት ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ አማካይነት ፡ የሚደረገው፡ ሙከራ ፡ ካልተሳካ ፡ አለቅጣት ፡ እንዲፋቱ ፡ ማድረጉ ፡ የሚሻል ፡ ሳይሆን ፡ ይቀራልን?

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ "የጋብቻን ፡ መፍረስ ፡ ማሰናከያ ፡ ዘዴዎቹ ፡" ሌላው ፡ ቢቀር ፡ በታወቁት ፡ ሀብታም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ላይ ፡ የተወሰነ ፡ ውጤት ፡ እንዳሳዩ ፡ ይነገራል ። ከቃል ፡ ተጠያቂዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አንደኛዋ ፤ ጋብቻቸው ፡ የፈረሰ ፡ እንደሆነ ፡ ሚስታቸው ፡ ብዙውን ፡ ንብረታቸውን ፡ ተካፍለው ፡ እንዳይወስዱባቸው ፡ በመፍራት፡ ከሚስታቸው ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ እንዲቀመጡ ፡ የተገደዱ ፡ ባለትዳር ፡ እንደምታውቅ ፡ ገልጻልናለች ።[95]

---

91. ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ ፡ የተጠቀሰው ፡ የሸዋ ፡ ልዑል ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ጉዳይ ።
92. የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ መምሪያ ፡ ተቀባይነት ፡ ቢያገኝ ፤ የሚቀጥለው ፡ ጥያቄ ፤ የግልግል ፡ ጉባኤው ፡ በሚደረግበት ፡ ወቅት ፡ ሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ የጋብቻውን ፡ መፍረስ ፡ አጥብቀው ፡ የሚፈልጉ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡ የሚለው ፡ ይሆናል ። ለዓይነት ፡ ካጠናናቸው ፡ የግልግል ፡ ጉዳዮች ፡ በአንደኛው ፡ ውስጥ ፡ ከቃል ፡ ተጠያቂዎቹ ፡ አንደኛው ፤ ሁለቱም ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ መፋታታቸውን ፡ የማይፈልጉ ፡ መሆናቸውን ፡ ቢናገሩም ፤ እውነተኛ ፡ ዓላማቸው ፡ ግን ፡ ይኸ ፡ አለመሆኑን ፡ ሊደርሱበት ፡ መቻላቸውን ፡ ገልጸዋል ። ይኸንንም ፡ ያደረጉት ፡ የንብረት ፡ ክፍያ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አንደኛውን ፡ ወገን ፡ መጥፎ ፡ ሁኔታ ፡ እንደሚገጥመው ፡ ሁለቱም ፡ ያውቁት ፡ ስለነበር ፡ ነው ፤ ብለዋል ።

ፒ ፡ ናይሽ ፤ "ሊቪንግ ፡ 'ሴፓሬት ፡ ኤንድ ፡ አፓርት" ፡ አዝ ፡ ኤ ፡ ግራውንድ ፡ ፎር ፡ ዲዞሊውሽን ፡ ኦፍ ፡ ማርየጅ ፡ ኢን ፡ አውስትራሊያ ፤" ጆርናል ፡ ኦፍ ፡ አፍሪካን ፡ ሎው ፤ ፯ኛ ፡ ቮልዩም ፤ ፲፱፻፶፱ ። በዚህም ፡ ደራሲው ፤ "ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ፳፬ ፡ የሚሆኑት ፡ የአሜሪካ ፡ ግዛቶች ፡ በሕግ ፡ መጽሐፍቶቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ የመሰሉ ፡ ሕጎች ፡ አሏቸው ፤" ሲሉ ፡ ገልጸዋል ። ከዚያው ፤ ገጽ ፡ ፪፻፳ ። እንግሊዝም ፡ በቅርቡ ፡ ይኸንኑ ፡ መከተል ፡ ጀምራለች ።
94. አር ፡ ዴቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፷ ።
95. የቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡ በጐ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ባልደረባ ፤ ከሆኑት ፡ ከወ/ሮ ፡ አልማዝ ፡ ዘውዴ ፡ ጋር ፡ ሚያዝያ ፡ ፲፬ ፤ ፲፱፻፹፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከተደረገ ፡ ውይይት ። ዳግም ፤ ለዓይነት ፡ ከተጠኑት ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፤ ባልየው ፡ ለመፋታት ፡ ያለውን ፡ ፍላጐት ፡ ካልተወ ፡ የንብረት ፡ ቅጣት ፡ እንደሚደርስበት ፡ ስለተነገረው ፤ እርቅ ፡ ሊደረግ ፡ መቻሉ ፡ ተገልጿል ።

## የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደገና ፡ መታየት ፤

ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሽማግሌዎች ፡ የተሰጡትን ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደገና ፡ ለማየትና፤ በአንዳንድ ፡ ሁኔታዎች ፡ ውስጥም ፤ በተለይም ፡ ውሳኔዎቹ ፡"ለሕግ ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ፡ ጠባይ ፡ ያላቸው ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ የተሰጡት ፡ ውሳኔዎች ፡ በግልጽ ፡ ከአእምሮ፡ ሚዛን ፡ ውጭ ፡" ሲሆኑ ፡ ውሳኔዎቹን ፡ ለመለወጥ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።[96] ብዙዎቹ፡ ይግባኞች ፡ በዚህ ፡ ክስ ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ይመስላሉ ። የተለመደው ፡ አቤቱታ ፤ የቀድሞው ፡ ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ስለንብረት ፡ ክፍያ ፡ ወይም ፡ ስለ ልጅ ፡ ማሳደጊያ ፡ የሰጡት ፡ ብይን ፡ ከአእምሮ ፡ ሚዛን ፡ ውጭ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ነው ።[97] የተለመደው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ መልስ ፡ ደግሞ ፤ የሽማግሌዎቹን ፡ ውሳኔ ፡ ከማጽደቁም በላይ ፤ የሚሰጠው ፡ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔ ፡ ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ ሊለወጥ ፡ አይገባውም ፡ የሚል ፡ ነው ።[98]

ሽማግሌዎቹ ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፤ ብዙ ፡ ባለጉዳዮች ፡ ስለንብረ ታቸው ፡ ክፍያ ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፤ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የንብረትን ፡ ክፍያ ፡ ጉዳይ ፡ ለመወሰን ፡ የሚችሉት ፡ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ብቻ ፡ መሆናቸው ፡ እየተነገራቸው ፡ ተመልሰዋል ።[99]

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፤ "የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ዳኞች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ " ይላል ።[100] በዚህ ፡ አን ቀጽ ፡ መሠረት ፡ ከዳኞቹ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚጠበቀው ፡ የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና፡ ዳኞቹን ፡ ውሳኔ ፡ ማጽደቅ ፡ ነው ። ይህ ፡ ዘዴ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ "የጋብቻን ፡ ፍቺ ፡ ማጽደቅ ፡"[101] ተብሎ ፡ ይጠራል ። ይህም ፡ ሽምግልናው ፡ ሲከናወን ፡ ተገቢውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተከትሏል ፡ አልተከተለም ፡ በማለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከሚሰጠው፡ ውሳኔ ፡ በላይ ፡ ምንም ፡ አይጨምርም ።[102] በዚህም ፡ ረገድ ፡ ዳኞቹ ፡ የሚመረምሩት ፡ ቀዋሚ ፡ ጥያቄ ፤ የመፋታትን ፡ ውሳኔ ፡ ከመስጠታቸው ፡ በፊት ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ባለትዳሮቹን ፡ ለማስታረቅ ፡ ሙከራ ፡ አድርገዋል ፡ አላደረጉም ፡ የሚለው ፡ ነው ። ዳኞቹ ፤ ከባለጉዳዮቹ ፡ አንደኛው ፡ በተለይ ፡ እስከጠየቃቸው ፡ ድረስ ፤ የንብረትንና፡ የሕፃናትን ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተውን ፡ የሽማግሌዎቹን ፡ መሠረታዊ ፡ ውሳኔዎች ፡ መመልከት ፡ የለባቸውም ።

---

96. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፯፻፴፯ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ፫፻፲፱/፩ ፫፻፶—፫፻፶፯ ።
97. ለምሳሌም ፡ የሰኔ ፡ ፲፬/፲፱፻፺፰ ፤ ውሳኔ ፤ (የከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ አሥመራ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ፡ ቁጥር ፡ ፺፪/፺፰) ፡ (ያልታተመ) ፡ (የቀድሞው ፡ ባል ፡ በንብረቱ ፡ ክፍያ ፡ ባለመስማማት ፡ ያመለከተበትን፡)ና፡ የግንቦት ፡ ፲፭/፲፱፻፺፱ዓ.ም ፡ ብይን ፤ (የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አዲስ ፡ አበባ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር፡ ይግ ባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፷፫/፺፱) ፡ (ያልታተመ) ፡ (የቀድሞዋ ፡ ሚስት ፡ የልጅ ፡ ማሳደጊያው ፡ ገንዘብ ፡ አንሶኛል ፡ በማለት ፡ ያመለከተችበትን) ፡ ይመለከቷል ።
98. ከዚያው ።
99. ለምሳሌም ፤ የጥቅምት ፡ ፫/፲፱፻፺፯ ፡ ፍርድ ፤ (የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አሥመራ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱/፺፯) ፡ (ያልታተመ)ና ፡ የነሐሴ ፡ ፲፬ቀ ፤ ፲፱፻፺፰ ፡ ፍርድ ፡ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ አሥመራ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫/፹፭ (ያልታተመ) ።
100. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፤ ቁጥር ፡ ፯፻፵፱ ።
101. ለምሳሌም ፡ የጀማነሽ ፡ አማረና ፡ የተፈራ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ ጉዳይ ፤ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፺፯ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፭/፺፯) ፡ (ያልታተመ) ።
102. የሸቶንና ፡ የሸቶን ፡ ጉዳይ ፤ (ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፺፩) የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ቮልዩም ፡ ፩ ፤ ገጽ ፡ ፩፻፺ ፡ ይመለከቷል።

ብዙዎቹ ፡ "የጋብቻን ፡ ፍቺ ፡ የማጽደቅ ፡" ጉዳዮች ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ የሆኑ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ዜጎችን ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።[103] በፍርድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ባልሆኑ ፡ ሰዎች ፡ አማካይነት ፡ የሚሰጠው ፡ የመፋታት ፡ ውሳኔ ፡ የሚደነቅ ፡ ቅንጅት፡ ቢሆንም ፤ በብዙ ፡ ሀገሮች ፡ ያልተለመደ ፡ ስለሆነ ፤[104] ውሳኔውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢያጸድቀው ፡ በውጭው ፡ ዜጋ ፡ ትውልድ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ የሚኖረውን ፡ ተቀባይነት ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይረዳል ።

<u>ስለ ፡ ቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ አበል ፤</u>

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ለድካማቸው ፡ ዋጋ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የታያቸውን ፡ አበል ፡ ሊወስኑ ፡ ይችላሉ ፡ ይላል ።[105] ምናልባት ፡ የዚህን ፡ አንቀጽ ፡ መኖር ፡ የሚያውቁት ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዚህም ፡ ቢሆኑ ፡ በባህልና ፡ በኩራት ፡ ስሜት ፡ ምክንያት ፡ የዚህን ፡ አበል ፡ መስጠትም ፡ ሆነ ፡ መቀበል ፡ አይፈቅዱም ። ለዓይነት ፡ ከተጠኑት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ከተመለከቷቸው ፡ ነገሮች ፡ በአራቱ ፡ ውስጥ ፡ ብቻ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ገንዘብ ፡ ተከፍሏቸዋል ።[106]

ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኝነት ፡ የሚመረጡት ፡ ዕጩዎች ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ጊዜያቸውን ፡ ማባከን ፡ የማይፈቅዱ ፡ ሆነው ፡ ከተገኙ ፤ (ይኸም ፡ በከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ እያደገ ፡ በመሄድ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ነው) ፡ ይህን ፡ አንቀጽ ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ማድረግ ፡ ለችግሩ ፡ በከፊል ፡ መፍትሔ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

ነገር ፡ ግን ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕጉን ፡ በማሻሻልም ፡ ሆነ ፤ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በሚያዘጋጁት ፡ መምሪያ ፤ የዚህን ፡ አበል ፡ ምንጭ ፡ መወሰን ፡ አስፈላጊ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። የአበል ፡ ክፍያ ፡ ከተደረገባቸው ፡ አራት ፡ ነገሮች ፡ መካከል ፡ በሦስቱ ፡ ውስጥ ፤ አበሉን ፡ የከፈለው ፡ ከሽማግሌዎቹ ፡ የጠየቀውን ፡ ሁሉ ፡ ያገኘው ፡ ወገን ፡ ነው ። ይህም ፤ የአበሉን ፡ ክፍያ ፡ ባለጉዳዮቹ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ በማድረግ ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ አደገኛ ፡ ሁኔታ ፡ ያመለክታል ። ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ከዚህ ፡ በተሻለ ፡ አኳኋን ፡ እንዴት ፡ መፈጸም ፡ እንደሚቻል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተቆጣጠረው ፡ በአራተኛው ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ታይቷል ። በዚህም ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፤ አበሉ ፡ የጋራ ፡ ሀብቱ ፡ ከመከፈሉ ፡ በፊት ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ተቀናሽ ፡ በማድረግ ፡ እንዲከፈል ፡ አድርጓል ።

ሌላ ፡ ተሰሚነት ፡ ያለው ፡ ዘዴ ፡ ደግሞ ፡ በሐረር ፡ በሚገኙ ፡ አንድ ፡ ጠበቃ ፡ የተሰነዘረው ፤ "በችግር ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሰዎችን ፡ መርዳት ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የተቀደሰ፡ ተግባር ፡ ነው ። ዳሩ ፡ ግን ፤ የግልግል ፡ ዳኝነት ፡ ጊዜያችንን ፡ በጣም ፡ የሚጠይቅ ፡ በመሆኑ ፤ መንግሥት ፡ ለዚሁ ፡ ሥራ ፡ የሚውል ፡ ጥቂት ፡ ገንዘብ ፡ ከበጀቱ ፡ ላይ ፡ ቢመደብ ፡ ይሻላል ፤" የሚለው ፡ አስተያየት ፡ ነው ።

---

103. ለምሳሌም ፤ ከዚያው ።

104. ተመሳሳይ ፡ ቅንጅቶች ፡ በብራዚል ፡ ውስጥና ፤ (አር ፡ ዴቪድ ፤ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የተጠቀሰው ፤ ገጽ ፡ ፳፬) ፡ በናይጀሪያ ፡ ይገኛሉ ። (ከላይ ፡ ማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፺ን ፡ ይመለከቷል) ።

105. የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፤ ቍጥር ፡ ፫፻፲፰/፫ ።

106. የግልግል ፡ ዳኝነት ፡ ጉባዔዎች ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ በተደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የምግብና ፡ መጠጥ ፡ ግብዣ፡ ነበር ።

በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙ ፡ አንድ ፡ የስልሳ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ አዛውንት ፡ ደግሞ፤ ይህንን ፡ ሃሳብ ፡ ጠለቅ ፡ ብለው ፡ በመመልከት ፤ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፤ በዚህ ፡ ጥናት ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የተገመተውን ፡ ብልህ ፡ አስተያየት ፡ ሰጥተዋል ፤

> "የግልግል ፡ ዳኝነት ፡ ስለክርስቶስ ፡ ተብሎ ፡ የሚደረግ ፡ በመሆኑ ፤ ለዚህ ፡ ተግባር ፡ ገንዘብ ፡ መቀበል ፡ ወይም ፡ መጠየቅ ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፤ መንግሥት ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ባለጉዳዮቹን ፡ ለማስታረቅ ፡ በቻሉ ፡ ቁጥር ፡ ገንዘብ ፡ ቢሰጥ ፡ አልቃወምም ።"

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚደረገው ፡ የጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ ችግርን ፡ በሽምግልና ፡ የማየት ፡ ተግባር ፡ መሠረታዊ ፡ ግብ ፡ ባለትዳሮቹን ፡ ለማስታረቅ ፡ የሚደረግ ፡ ሙከራ ከሆነ ፤ ምንኛ ፡ የሚደነቅ ፡ ሃሳብ ፡ ነው !